# የቃል ክርክር አቀራረብ ዘዴዎች
# (Oral Trial Techniques)

መስከረም-2006 ዓ/ም

<u>አዲስ አበባ</u>

## ማውጫ


1. መግቢያ ...................................... 3
2. የፍርድ ሂደት ............................... 8
3. የቃል ክርክር ክህሎት የስነምግባር ጉዳዮች......................................... 15
4. ለፍርድ ሂደት መዘጋጀት .................. 22
5. የመክፈቻ ንግግር ............................ 29
6. ዋና ጥያቄ .................................... 34
7. መስቀልኛ ጥያቄ .............................. 41
8. የመዝጊያ ንግግር ............................ 52
9. የመቃወሚያ ነጥቦች........................ 57
10. አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ......... 65
11. የምርመራ ሰነዶች ............................ 69
12. ዋቢ ጽሁፎች .................................. 75

## መግቢያ

ይህንን ጽሁፍ ማዘጋጀት ያስፈለገበት በፍትህብሄርም ሆነ በወንጀል የፍትህ አስተዳደር ያለው የቃል ክርክር ሁኔታ በሚፈለገው መልኩ እየተካሄደ ባለመሆኑ ችግሩን በስልጠና መቅረፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አካላት የተደረጉ ጥናቶችና የስራ እንቅስቃሴዎች የችግሩን አሳሳቢነት በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡ ለምሳሌ በፌደራል ፍትህ አካላት ባለሞያዎች ስልጠና ማእከል ለ2005 የስራ ላይ ስልጠና በ2004 በተደረገው የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የቃል ክርክር ክህሎት ( oral trial techniques ) አስፈላጊነት በመታወቁ ስልጠናው በተወሰነ መልኩ ቁጥራቸው 160 ለሚሆኑ ዳኞችና አቃቤያነህግ ስልጠናው እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ፍትህ ለሁሉም ፕሪዝን ፎሎው ሺፕ ኢትዮጵያ ከፍርድ ቤቶች ጋር በመሆን በአደረገው ጥናት በክርክር ክሁሎት ዙሪያ ያለው ችግር በመታወቁ፤ካናዳ አገር ከሚገኘው የፍትህ ትምህርት ማህበረሰብ (justice Education Society) ከተባለ ድርጂት ጋር በመተባበር 20 ለሚሆኑ ዳኞች፣አቃቤያነህግና በስልጠና መአከላት ለሚገኙ ባለሞያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት 100 ለሚሆኑ ዳኞችና አቃቤያነህግ ስልጠናውን ሰጥቷል፡፡ የፍትህ ሚኒስቴር ከአምስተረዳም ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለ200 ለሚሆኑ አቃቤያነህግ ስልጠና ለመስጠት እቅድ በመያዝ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ በዚህ ሁሉ ጥረት የተከናወነውን ተግባር በስልጠናው የተሳተፉትን ባለሞያዎች ቁጥር በፍትህ ስርአቱ ካለው የሰው ሀይል ቁጥር ጋር ስናነጻጽረው እዚህ ግባ የሚባል አይሆንም፡፡

የጽሁፉ አላማ በፍትህ ስርአቱ ውስጥ ተሰማርተው የሚያገለግሉ ዳኞች፣አቃቤያነ ህግ እና ተከላካይ ጠበቆች ተገቢ የቃል ክርክር ክህሎት በማግኘት ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ ስራ እንዲያከናውኑ ማስቻል ነው። ለዚህም ሲባል ጽሁፉ በቃል ክርክር ሂደት ሊነሱ የሚገባቸውን አብይ ጉዳዮች አካቶ የያዘ ሲሆን፤ሰልጣኞቹ የራሳቸውን ልምድና ተሞክሮ በማቅረብ የተሟላ እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙም አሳታፊነትንና ልምምድን መሰረት ያደረገን የማስተማርያ ዘዴን መሰረት ያደረገ ነው።

የስልጠና ጽሁፉ ዘጠኝ ርእሰ ጉዳዮችን ያካትታል። የመጀመርያው ርእሰ ጉዳይ በጠቅላላው የክርክር ሂደት ምንድን ነው በሚለው ዙርያ የሀገራችንንና የሌሎች ሃገሮችን አሰራር የሚያሳይ ነው። በዚህ ርእሰ ጉዳይ የአድቨረሳርይል እና የኢንኩሲቶርያል የፍርድ ሂደት ስርአቶች የሚጠቀሱ ሲሆን፤የሀገራችን የህግ ስርአት ምን አይነት አቅጣጫ እነደያዘና ከእነዚህ የፍርድ ሂደት ስርአቶች የሚያመሳስለውና የሚያለያየው ጉዳይ ምን እንደሆን ይዳሰሳል።

ሁለተኛው ርእሰ ጉዳ የሚያጠነጥነው በክርክር ሂደት በክርክሩ ሂደት የሚሳተፉ ወገኖች ምን አይነት ስነምግባር ሊኖራቸው እንደሚገባ ያስረዳል። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ሁለት አብይ ጉዳዮች ይዳሰሳሉ። አንደኛው በክርክር ሂደት ሊከበሩና ሊተገበሩ የሚገባቸው የስነምግባር መረሆች ምም ናቸው የሚል ነው። ሁለተኛ ጉዳይ ደግሞ እነዚህን የስነ ምግባር መርሆዎች በማክበር የምናገኘው እሴት ምንድን ነው የሚለውን የሚመለከት ነው።

ሦስተኛው ርእሰ ጉዳይ የሚያተኩረው ለፍርድ ሂደት በሚደረግ ዝግጅት ላይ ነው። ወታደራዊ ጠበብቶች የልምምዱ ከባድነት ውጊያውን ቀላል ያደርገዋል በማለት ይገልጹታል። አባባሉ በወታደራዊ ሰዎች ዘንድ የተገለጸ ቢሆንም፤ለማናቸውም የሙያ መስክ አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም። ክርክር በፍትህ አስተዳደር ስርአት ውስጥ ትልቁን ስፍራ የሚይዝና በመጨረሻም የሚተላለፈው ውሳኔ በዚህ ሂደት ላይ የሚመሰረት በመሆኑ ተገቢ ዝግጅትና ልምምድ ማድረግ ለውጤታማነት ወሳኝ ነው።

አራተኛው ርእሰ ጉዳይ የሚያተኩረው በመክፈቻ ንግግር ላይ ነው፡፡ የመክፈቻ ንግግር አጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ምን እንደሚመስልና ክርክሩን ለማስረዳት የሚቀርቡ ማስረጃወች እንዴትና በምን መልኩ የቀረበውን ክርክር እንደሚያስረዱ የሚያመላክት በመሆኑ በክርክሩ ሂደት ለሚሳተፉ ሁሉም ወገኖች ተገቢ ግንዛቤ በመፍጠር የየራሳቸውን ተግባር በመረዳት ስራቸውን እነዲያከናውኑ ስለሚያግዝ የጉዞ ካርታ (road map) ተብሎ የታወቃል፡፡

አምስተኛው ርእሰ ጉዳይ ዋና ጥያቄ የሚቀርግበትን ይመለከታል፡፡ ከክርክሩን እንዲያስረዳ የተፈቀደለት ወይም የታዘዘ ወገን ለጠራቸው ምስክሮች ዋና ጥያቄ ያቀርባል፡፡ በዚህ ምእራፍ ተከራካሪው ወገን እንዴት አድርጎ ምስክሮቹን እንደሚጠይቃቸውና ሊከተላቸው የሚገባቸው መርሆዎች ምን ምን እንደሆኑ ይብራራል፡፡ ለክርክሩ ማቆሚያ የሆኑ መሰረቶች የሚጣሉት በዚህ ደረጃ ላይ በመሆኑ ምስክሮችን የሚጠራው ወገን ምን ማድረግ እንዳለበትም ተገቢ ግንዘዛቤ ያገኛል፡፡

ስድስተኛው ርእሰ ጉዳይ የሚመለከተው መስቀልኛ ጥያቄን ነው፡፡ ምስክር ያቀረበው ወገን አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ማስረጃው የቀረበበት ሌላኛው ወገን መስቀልኛ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ በዚህ ደረጃ መስቀልኛ ጥያቄ የሚቀርበው በዋና ጥያቄ በምስክሩ የተነገረው ሀሳብ ትክክል አለመሆኑን፣በሃሰት የተነገረ መሆኑን ወይም አጠራጣሪ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ውጤታማ የሆነ መስቀልኛ ጥያቄ እንዴት አድርጎ መቅረብ እንዳለበት ይገለጻል፡፡

ሰባተኛ ርእሰ ጉዳይ ሆኖ የሚቀርበው የመዝጊያ ንግግር ነው፡፡ የመዝጊያ ንግግር በተለምዶ የመፋረጃ ሀሳብ በማለት የምንጠራው ነው፡፡ የመፋረጃ ሀሳብ በክርክርና በማስረጃ ውስጥ ያሉትን ክፍተቶችና አጠራጣሪ የሆኑ ነጥቦች በማብራራትና ግልጽ በማድረግ ፍርዱን ለሚሰጠው አካል በሚያሳምን መልኩ የሚቀርብ የማሳረጊያ ክርክር ነው፡፡ በተግባር የመፋረጃ ሀሳብ ተብሎ የሚነገረው የቃሉ ትርጉም ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ አፈጻጸሙም ከህጉ መንፈስ የወጣ በመሆኑ በዚህ ምእራፍ ጽንሰ ሀሳቡ በአግባቡ ይገለጻል፡፡

ስምንተኛው ርእሰ ጉዳይ ማስረጃን በሚለከት የሚቀርቡ መቃወሚያዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ማስረጃ ተመዝኖ ለማናቸውም ውሳኔ መሰረት የሚሆነው በመጀመርያ ቀርቦ መሰማት ሲችል ነው፡፡ በመሆኑም ማናቸውም ተከራካሪ ወገን የሚያቀርበው ማስረጃ መታየት ወይም መሰማት ያለበት መሆን አለበት፡፡ አንዳንድ ጊዜ ተከራካሪዎች በማወቅም ሆነ ባለማዎቅ የሚያቀርቀቧቸው ማስረጃዎች ወይንም ነጥቦች ተገቢ ሆነው ካልተገኙ በሂደቱ ሊጎዳ የሚችለው ወገን መቃወሚያ እንዲያቀርብ ህግ ይፈቅድለታል፡፡ ፍርድ ቤቱም ክርክሩን ወዲያውኑ ተመልክቶ ተገቢ ትእዛዝ መስጠት አለበት፡፡

በመጨረሻም አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ተለይተው የተቀመጡ ሲሆን፤ጽሁፉን የሚያነበው ወገን ህጎቹን ለማገናዘብ ሌላ ሰነድ ከሚያገላብጥ ይልቅ በቀላሉ መጠቀም እንዲችል ታስቦ የተደረገ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሰልጣኞች ስልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ እራሳቸውን በሚከተሉት ሆኔታዎች መለካት ይችላሉ፡፡

- ስለክርክር ሂደት ተገቢ ግንዛቤ ያገኛሉ፤በአገኙት ግንዛቤ ስራቸውን ማከናወን ይችላሉ፡፡
- ለክርክር ተገቢ ዝግጅት ማድረግ ውጤታማ ለመሆን እንዴት እንደሚያስችል አውቀው፤ከልማዳዊ አሰራር በመላቀቅ እራሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡
- የሚያቀርቧቸውን ምስክሮች እንዴት ማዘጋጀት፣እንዴት መጠየቅ፣በሌላው ተከራካሪ ወገን የሚቀርበውን የማስተባበያ ጥያቄ እንዴት መገመት እንደሚችሉ ይረዳሉ፡፡

- በቀረበባቸው ማስረጃ የተገለጸው ፍሬ ነገር ሀሰት መሆኑን፣አጠራጣሪ መሆኑን ወይም ትክክል አለመሆኑን ማሳየት እንዴት እንደሚችሉ አውቀው በአግባቡ ስራ ላይ የሚያውሉበትን እውቀት ይጨብጣሉ፡፡
- በአቀረቡት ክርክር ወይንም ማስረጃ ግልጽ ያልሆነውን ፍሬ ነገር ወይም ክፍት ሆኖ የሚታየውን ጉዳይ በሚያቀርቡት የመዝጊያ ንግግር እንዴት ማቅረብ እንደሚችሉ ይገነዘባሉ፡፡

# አንድ

## የፍርድ ሂደት (Trial)

የፍርድ ሂደት በፍርድ ቤት የክስ አቤቱታ ከቀረበበት እስከ ጉዳዩ እልባት እስከሚያገኝበት ድረስ ያለውን ስራ የሚመለከት ነው፡፡ ጽሁፉ የሚመለከተው ርእሰ ጉዳይም የሚያጠነጥነው በዚሁ ሂደት ዉስጥ በሚከናወኑ ተግባት ላይ ነው፡፡ በክርክር ክህሎትን የሚነሱ ነጥቦችን በአግባቡ ለመረዳትና ለመፈጸም የፍርድ ሂደቱን አደረጃጀትና የሚከተላቸውን መርሆዎች ማወቅ ይገባል፡፡ በየሀገሩ የሚኖረው የፍርድ ሂደት እንደየሀገሩ የኢኮኖሚ እድገትና የታሪክ ሁኔታ ይለያያል፡፡ በየትኛውም የህግ ስርአት የሚኖር የፍርድ ሂደት ክርክርን የሚያስተናግድ ቢሆንም፤ስርአቱ በሚከተለው መርህ ምክንያት የክርክሩ አካሄድ ሊለያይ ይችላል፡፡ በመሆኑም በሀገራችን የፍርድ ሂደት የሚካሄደውን ክርክር ለመለየት የሃገራችን የህግ ስርአት የተመሰረተበትን መርህ ማወቅ ይገባል፡፡

የሀገራችንን የህግ ስርአት ለመረዳት በሌሎች ሀገሮች ያሉ ስርአቶችን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ የሁሉንም ሀገሮች የህግ ስርአቶችን በዝርዝር ለማስቀመጥ ባይቻልም፤ብዙ ሀገሮች በአንድነት የሚገኙበትን የህግ ስርአት በማየት የራሳችንን በንጽጽር ለመረዳት እንችላለን፡፡ በአለም ላይ ታዋቂ የሆኑት የህግ ስርአቶች ሁለት ናቸው፡፡ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአለም ላይ የሚገኙ ሀገሮች ከነዚህ የህግ ስርአቶች ጋር የሚገናኙበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት በአንድ በኩል አንዳንድ የህግ መርሆዎች አለም አቀፍ ባህሪ ስላላቸው (Generaly accepted principles) በሌላ በኩል ሀገሮች በአንድ ወቅት ከነበራቸው የጋራ ግንኙነት አንጻር የሚፈጠር ነው፡፡ አብይ ተብለው የሚታወቁት የህግ ስርአቶች ተከራካሪ ወገኖችን ማእከል ያደረገ (adversarial) እና ችሎቱን ማእከል ያደረገ (inquisitorial) በመባል ይታወቃሉ፡፡

ተከራካሪ ወገኖችን ማእከል ባደረገው የህግ ስርአት ማስረጃ በማቅረብና ማስረጃን በማሰማትና በመመርመር ያለው ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ የሚወድቀው በተከራካሪ ወገኖች ላይ ነው። ዋናው ሃሳቡም በሁለት ወገኖች ግልጽ የሆነ ክርክር ከተደረገ እውነት ሊረጋገጥበት የሚችልበት ዕድል የሰፋ ነው የሚል ነው። ይህ የክርክር ስርአት የኮመን ላው የህግ ስርአትን በሚከተሉ ሀገሮች የሚሰራበት ነው። በዚህ ስርአት የዳኞች ሚና የክርክሩን ሂደት መምራትና መቆጣጠር ነው። አልፎ አልፎ በዳኞች በኩል ለምስክሮች የሚቀርብ ጥያቄ ካለም የሚቀርበው ግልጥ ያልሆኑ ነገሮችን ለማብራራት እንጅ ሌላ ባህሪ የለውም። በዚህ ስርአት ምስክሮችን የማቅረብና የመመርመር ሃላፊነት የሚወድቀው በተከራካሪ ወገኖች ላይ ብቻ በመሆኑ ካያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል የሚለው የሀገራችን አባባል ሙሉ በሙሉ ይሰራል። አሜሪካ፤እንግሊዝና ካናዳን የመሳሰሉ አገሮች በዚህ ስርአት የሚገኙ ናቸው።

ችሎትን ማእከል ያደረገው አሰራር የሲቪል ሎው የህግ ስርአትን በሚከተሉ ሀገሮች የሚተገበር ነው። በዚህ ስርአት ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ከማቅረብ የዘለለ ወሳኝ ሚና የላቸውም። ምስክሮችን በመጠየቅና በመመርመር እረገድ ሃላፊነቱን የሚወጣው ፍርድ ቤቱ ነው። ፍርድ ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘው ስለጉዳዩ ምስክሮችን ለመጥራት ይችላል። የዚህ ስርአት የአስተሳሰብ መነሻው ትክክለኛውንና እውነተኛውን ነገር ለማግኘት ገለልተኛና እስከመጨረሻ የሚደረግ ምርመራ (impartial and exhaustive investigation) አስፈላጊ ነው የሚል ነው። ገለልተኛና ጥልቀት ያለው የምርመራ ሂደት የሚጀምረው ከፍርድ ሂደት በፊት በመርማሪ ዳኛ (examining magistrate) ሲሆን፤በመቀጠልም በፍርድ ሂደት ዳኛም (trial judge) ተጠናክሮ የሚከናወን ነው። አንዳንድ ጊዜም በምርመራው ጊዜ የነበረው ዳኛ በፍርድ ሂደቱም ጉዳዩን ሊመለከተው ይችላል።

የሀገራችንን የክርክር ስርአት በምንመለከትበት ጊዜ በአንዳንድ የህግ ባለሞያዎች አካባቢ የሀገራችንን የህግ ስርአት ከሁለቱ የህግ ስርአት ከአንደኛው ጋር የማያያዝ ሁኔታዎች ይስተዋላሉ፡፡ የኛ የክርክር ስርአት ምን ይመስላል የሚለውን ለማወቅ በስነ-ስርአት ህጎቻችን የተቀመጡትን ክርክር የሚመራባቸውን የህግ ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በወንጀለና መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ከቁጥር 136-148 እና በፍትሀብሄር ስነ-ስርአት ህግ ከቁጥር 257-273 ያሉት ድንጋጌዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ናቸው፡፡ ከነዚህ የህግ ድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው ተከራካሪ ወገኖችም ሆኑ ፍርድ ቤት ምስክሮችን በማቅረብና በመመርመር ተገቢ ሚና እንዳላቸው ነው፡፡ በእርግጥ ምስክሮችን በማቅረብና በመመርመር የተካራካሪዎቹ ድርሻ የጎላ ቢሆንም፤ፍርድቤት ያለውም ድርሻ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ፍርድ ቤት በማናቸውም ጊዜ ማናቸውንም ዓይነት ጥያቄ ማቅረብ እንደሚች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 136(4) እና በፍትሀብሄር ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 261(4) ላይ በሚገባ ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡ ፍርድ ቤት ክርክሩን በሚመለከት የራሱን ምስክሮች መጥራት እንደሚችል ደግሞ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 143 እና በፍትሀ ብሄር ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 264 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የሀገራችን የህግ ስርአት ተከራካሪ ወገኖችን እና ፍርድ ቤትን ምስክሮችን በማቅረብና በመመርመር ተገቢ ድርሻ እንዲኖራቸው የሚያደርግ በመሆኑ ተከራካሪ ወገኖችን ማዕከል ካደረገውና ፍርድ ቤትን ማዕከል ካደረጉት የህግ ስርአቶች ይለያል፡፡

በሃገራችን የስነ-ስርአት ህጎች ፍርድ ቤቱ ትክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መስሎ ሲታየው በማናቸውም ጊዜ የቀረበውን ምስክር ማናቸውንም ዓይነት ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፡፡ የህጉ መንፍስ ምን እንደሆነ መገመት ቢቻልም ህጉን መሰረት አድርጎ የጥያቄውን ዓይነትና የሚቀርብበትን ጊዜ መገደብ ስለማይቻል፤ አንዳንድ ጊዜ ፍርድቤቶች ወደአንደኛው ወገን ያዘመመ እስከሚመስል ጥያቄዎችን ስለሚያቀርቡ በፍርድ ቤቶች ነፃነትና ገለልተኝነት ላይ ትችቶች ሲቀርቡ ይስተዋላሉ፡፡ እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎች ሊከሰቱ የሚችሉት ፍርድ ቤቶች

ለአንደኛው ወገን አድልተው በመስራታቸው ሳይሆን፤ጉዳዮችን በማጣራት ሂደት እስከ ተካራካሪ ወገኖች ድርሻ ድረስ በመግባት በሚታዩ ሁኔታዎች ነው (ይህንን በሚመለከት ጸሀፊው ተገቢውን ግንዛቤ መጨበጥ የቻለው በተለያዩ ስልጠናዎች ከስልጠና ተሳታፊዎች በመረዳት ነው)፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 9 (4) መሰረት ሀገራችን ያጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ካጸደቀቻቸው ስምምነቶች አንዱ ደግሞ አለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ ስምምነት (ICCPR) ነው፡፡ በዚህ አለም አቀፍ ስምምነት አንቀጽ መሰረት ማንኛውም ሰው ነፃና ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል የመዳኘት መብት አለው፡፡ ፍርድ ቤቶችም ነፃና ገለልተኛ ሆነው የመስራት ግዴታ አለባቸው፡፡ ስራቸውን በሚያከናውኑበት በማናቸውም ጊዜ በፍርድ ቤቱ ነፃነትና ገለልተኝነት ላይ ጥያቄ ሊያስነሳ ከሚችል ተግባር ሊቆጠቡ ይገባል፡፡ የፍርድ ቤቶች ነፃነትና ገለልተኛነት የሚረጋገጠው በተገልጋዩ እይታ በመሆኑ ስለራሳችን የምናውቀውን ብቻ ሳይሆን ጉዳዩ በሌሎችስ ዐይን እንዴት ይታያል የሚለውን መመልከት ይገባል፡፡ በመሆኑም በስነ-ስርአት ህጎቻችን የተሰጡ ምስክርን የመመርመርና የመጠየቅ የፍርድ ቤት ስልጣን ስራ ላይ በምናውልበት ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡

በክርክር ጊዜ ሌላው የሚነሳው ነገር የህግ ስርአታችን ከማስረጃ አሰባሰብ ጋር በተያያዘ የሚከተለውን አካሄድ ነው፡፡ በፍርድ ሂደት ማስረጃን በሚመለከት ተፈጻሚነት ያላቸው የስነ-ስርአት ሞዴሎች (የወንጀል ስነ-ስርአትን የሚመለከት ነው) አሉ፡፡ እነዚህን ሞዴሎች ማወቅ በህግ ጽሁፍ (legal literature) እና በእራሳችን የህግ ስርአት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት አውቀን በህግ መሰረት ብቻ ለመስራት እንድንችል ይረዳናል፡፡ ይህንንም ለማለት የሚያስችለን በተግባር በህጉና በህግ ጽሁፍ መካከል ያለውን ልዩነት የመቀላቀል ሁኔታ ስለሚታይ ነው፡፡ (ጸሀፊው ይህንን የተገነዘበው በዳኝነት፣

በዐቃቤህግነት፣በአስተማሪነትና በአሰልጣኝነት በሚሰራበት ጊዜ ነው፡፡) በመሆኑም ሞዴሎቹን ማየት እና የኛ ምን ይመስላል የሚለው ማወቅ በማስረጃ ላይ የምናቀርበውን ተቃውሞ በህግ ብቻ መወሰን እንድንችል ስለሚያስችለን አንዳንድ ነጥቦችን እናነሳለን፡፡

የወንጀል የፍትህ አስተዳደር ሞዴሎችን በተመለከተ ሁለት ዓይነት ሞዴሎች አሉ፡፡ እነዚህም በህግ መሰረት የማከናወን ሞዴል (due process model) እና ወንጀል በመከላከል ላይ ያተኮረ ሞዴል (crime prevention model) ተብለው ይታወቃሉ፡፡ የመጀመርያው ሞዴል መሰረታዊ አስተሳሰብ አንድን ወንጀል ለማጣራትና ለማስረዳት የምንጠቀምበት ዘዴ ህግን ብቻ መሰረት ማድረግ አለበት፡፡ ወንጀሉን ለማረጋገጥ የሚረዳንም ቢሆንም እንኳ በህግ መሰረት ያልተገኘን ማስረጃ መጠቀም የለብንም፡፡ የመርዛማ ዛፍ ፍሬ መርዛማ በመሆኑ ፍትህን ለማከናወን ልንጠቀምበት አይገባም የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ሞዴል ደግሞ የወንጀል የፍትህ አስተዳደር ዋና ተግባር ወንጀልን መከላከል ነው፡፡ የምንሰበስበው ማስረጃ ወንጀሉን ለማረጋገጥ እስከረዳን ድረስ የተሰበሰበበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት አይገባም፡፡ ምአልባት ማስረጃው ህግን በመተላለፍ የተገኘ ከሆነም ህግን በመተላለፍ ያመጣውን ሰው ወይም አካል በህግ ከመጠየቅ በስተቀር በዚህ ምክንያት ማስረጃውን ውድቅ ማድረግ አይገባም የሚል ነው፡፡

ወደሀገራችን የወንጀል የፍትህ አስተዳደር ስርአት ስንመጣ ስርአታችን የትኛውን ሞዴል ይመስላል የሚለውን ለመወሰን አግባብነት ያላቸው ህጎች የወንጀለኛ ስነ-ስርአት ህግና ህገ-መንግስታችን ናቸው፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህጉ ከማስረጃ አሰባሰብ (የተከሳሽን ቃል በመቀበል፣የምስክርን ቃል በመቀበል፣ብርበራና መያዝን በሚመለከት) ጋር ተያያዥነት

ያላቸውን ድንጋጌዎች ስንመለከት አለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ መከናወን እንዳለባቸው የሚያዙ ናቸው፡፡ በእርግጥ የስነ-ስርአት ህጉ ከሚደነግገው ውጭ ማስረጃው ቢገኝ ምን የሆናል ለሚለው ግልጽ ድንጋጌ አናገኝም፡፡ ነገር ግን ማስረጃዎችን እንዴት አድሶ ማሰባሰብ እንደሚቻል የተቀመጠው፤ ህግን መሰረት አድርጎ መከናወን እንዳለበት ስለሚያሳይ የስርአቱን አቋም በሚገባ መረዳት ይቻላል፡፡ በህገ-መንግስቱም ስለሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተገለጸው በጠቅላላ፤ስለተያዙና ስለተከሰሱ ሰዎች የተደነገገው በነጠላ በህገ-መንግስቱ ስርአት ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው የህግ የበላይነትን አክብሮ መኖር እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም በሀገራችን ያለው የወንጀል የፍትህ አስተዳደር የሚመራባቸው የህግ ማእቀፎች ህግን መሰረት በማድረግ መስራት እንደሚገባ ስለሚያዙ የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው የሚለውን አስተሳሰብ ስርአታችን አይቀበልም፡፡

በአጠቃላይ በሀገራችን የፍርድ ሂደት በሚከናወንባቸው የስነ ስርአት ዓይነቶችና ሞዴሎች ላይ ተገቢ ግንዛቤን መጨበጥ ክርክርን ለማቅረብና በሂደቱ የሁሉንም ወገን ሚና ምን እንደሚመስል በማወቅ ተግባራችንን በተገቢው ሁኔታ ለመወጣት ይረዳል፡፡ አንዳንድ ጊዜም በህግ ባለሞያዎች ዘንድ እንደሚስተዋለው፤ከተለያዩ የህግ ጽሁፎች የተረዳናቸውንና የተገነዘብናቸውን ጠቅላላ እውቀቶች ከራሳችን የህግ ስርዐት ጋር ደምሮ የማየት አካሄድ አለ፡፡ በእርግጥ ህጋችን ግልጽ ባልሆነበት ጊዜና ህጉን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤በታወቁ የህግ ሁፎች ላይ የሚገኙ ጽንሰ ሀሳቦችን ክፍተቱን ለመሙላት መጠቀሙ አይከፋም፡፡ ነገር ግን ይህም ቢሆን በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን የህግ ስርአቱን መሰረትና ታሪካዊ አመጣጥ መመልከት ይገባል፡፡ ከዚህም አንጻር ከላይ ለመመልከት የሞከርናቸው ሀሳቦች እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎችም ባጋጠሙ ጊዜ እንዴት አድርገን ያሉብንን ችግሮች መፈታት እንዳለብን መጠነኛ የሆነ ግንዛቤን ይፈጥሩልናል፡፡

## መልመጃዎች

(1) የፍርድ ሂደቶች ነፃና ገለልተኛ ሆነው መከናዎን አለባቸው፡፡ በሀገራችን ህጎች ዳኞች በማናቸውም ጊዜ ማንኛውንም አይነት ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችሉና ማስረጃ መጥራት እንደሚችሉ ተጠቅሷል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎችና ማስረጃዎች ወደአንደኛው ወገን የማጋደል ሁኔታ ስለሚስተዋልባቸው በፍርድ ቤቶቸ ነፃነትና ገለልተኛነት ላይ ጥርጣሬን ሲፈጥር ይታያል፡፡ በእርስዎ አስተያየት ፍርድ ቤቶች ሀላፊነታቸውን በትክክል ለመወጣት ተግባሩን በምን አይነት መልኩ ማከናዎን አለባቸው ይላሉ?

(2) ማስረጃ በሚሰማበት ጊዜ ከሚቀርቡ ክርክሮች አንዱ በማስረጃ ላይ የሚቀርብ ነው፡፡ እርስዎ ዳኛ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ የቀረበው ማስረጃ በህገወጥ ድርጊት የተገኘ በመሆኑ ሊቀርብ አይገባም የሚል ተቃውሞ ቢቀርብ ምን ውሳኔ ይሰጣሉ?

## ሁለት

## የቃል ክርክር ክህሎት የስነ ምግባር ጉዳዮች

የፍትህ ስራ ስነ ምግባር ከሚገለጽባቸው የስራ ሂደቶች አንዱና ዋንኛው ክርክር ነው። በዚህ ሂደት የሚሳተፉት ሰዎች የህግ ባለሞያወች ቢሆኑም ከተሰማሩበት የስራ መስክ አንጻር የየራሳቸው የሆነ ባህሪ ሊኖራቸው ይችላል። በዚህ ጽሁፍ ለመታየት የተፈለገው ጉዳይ የእየአንዳንዱን ባለሙያ ስነምግባር ዝርዝር ሳይሆን፤አንድን የክርክር ሂደት ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ ከእየአንዳንዱ ባለሙያ ምን ይጠበቃል የሚለው ነው። በዚህ ሒደት የሚሳተፉት ዳኞች፣ጠበቆችና አቃቤያነህግ ሲሆኑ ሁሉም በየበኩሉ ሊከተለውና ሊያከብረው የሚገባውን ነገር ለማሳየትና ለመግለጽ ይሞከራል። መሰረታዊ የሆኑ የስነ ምግባር መርሆችንንም ከማየታችን በፊት ስነ ምግባር ስላለው እሴት በመጀመርያ እንመለከታለን።

**(ሀ) ዉጤታማነት-** ማናቸውም ተግባር የሚለካው በውጤት ነው። አንድን የስራ እንቅስቃሴ በትክክል አከናውነናል ለማለት የሚቻለው ስራውን ከተለያዩ መመዘኛወች አንጻር በመመዘን ጥሩ ውጤት ማምጣት ስንችል ነው። ስራው በምን ያህል ጊዜ፣በምን ያህል መጠን፣በምን ያህል ወጭና እንዴት ባለ ጥራት ተከናውኗል የሚለው ስራ የሚመዘንበት ስርአት ነው። የአንድ የፍትህ ስርአት የስነ ምግባር እሴት ከሚገለጽባቸው ሁኔታዎች አንዱ ዉጤታማነት ነው። አንድ የክርክር ሂደት ውጤታማ ነው የሚባለውም ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ፣በመጠነኛ ወጭ፣ደረጃውን በጠበቀ ጥራትና በተፈለገው መጠን ተከናውኖ ሲገኝ ነው። በመሆኑም የክርክር ሂደት ቀልጣፋ፣ወጭ ቆጣቢ፣ጥራትን ለድርድር የማያቀርብና በተገቢ ብዛት ተፈጽሞ መገኘት አለበት። ይህንንም ለማድረግ ባለሞያዎቹ ካላቸው እውቀትና ክህሎት በተጨማሪ መሰረታዊ የስነ ምግባር መርሆችን በሚገባ ማወቅና ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል።

(ለ) ተገማችነት- የስነ ምግባር መርሆዎችን እንድናከብር የሚፈለግበት ሌላኛው ምክንያት የፍትህ ስርአቱ ተገማች እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡ የመልካም አስተዳደር እሳቤዎች በህዝቡ ዘንድ ከመድረሳቸውና ከመታወቃቸው በፊት ስለተገማችነት የነበረው አስተሳሰብ ለየት ያለ ነበር፡፡ በሀገራችን እንደሚታወቀው‹‹ፍርድና ጥራቢ የሚወድቅበት አይታወቅም›› የሚል አስተሳሰብ ነበር፡፡ የዚህ አይነቱ አስተሳሰብ በእኛ ሀገር ብቻ የነበረ ሳይሆን ተመሳሳይ ማህበራዊ አመለካከት በነበሩባቸውም ጊዜ ዛሬ በመልካም አስተዳደር ተምሰሌት በሆኑ አገሮችም ጭምር ይንጸባረቅ ነበር፡፡ ለምሳሌ እንግሊዝን በመሳሰሉ ሀገሮች ቀደም ሲል በነበሩ ጊዚያት ‹‹ justice is what ajudge has in his breakfast›› የሚል አባባል ነበር፡፡ ይህ አባባል ከአማረኛው አነጋገር ጋር በቃላት አጠቃቀም የሚለያይ ቢሆንም በይዘት ግን አንድኛው የሌላውን ሀሳብ የሚገልጥ ሆኖ ይገኛል፡፡

ፍርድም ሆነ ፍትህ የመልካም አስተዳደር በሰፈነበት ህብረተሰብ ውስጥ ምን መሆን እንዳለበት ለመገመት አያዳግትም፡፡ የህግና የፍትህ ስርአቱ በህግ መሰረት ብቻ እስከሰራ ድረስ በአንድ ነገር የተያዘ ክርክር ምን ውጤት ይኖረዋል ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ያንን ያህል አወዛጋቢ ሁኔታ የሚፈጥር አይሆንም፡፡ ማንም ህጉንና የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ የሚያውቅ ሰው ውጤቱ ምን እንደሚሆን መገመት አያዳግተውም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድንበር ላይ ያሉ ጉዳዮችን ለመወሰን ግለሰባዊ አመለካከትን ሊፈልግ ይችላል፡፡ እንደነዚህ የመሳሰሉት ነገሮች ግን የሚፈጠሩት አልፎ አልፎ በመሆኑ፤በመርህ ደረጃ ልናስተናግዳቸው አንችልም፡፡ በመሆኑም ተገማችነትን በሚመለከት የሚታዩ ችግሮች ከስነምግባር ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ተገማችነትን እውን ለማድረግ የስነ ምግባር መርሆዎችን ማክበርና ስራ ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡

(ሐ) ተደራሽነት- የተደራሽነት ችግር በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡፡ ህብረተሰቡ በመሰረተ ልማት አለመሟላት የሚያገኘው የፍትህ አገልግሎት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ አይነቱ

የተደራሽነት ችግር ከስነምግባር ጋር የሚያያዝ አይሆንም፡፡ ነገር ግን በመስኩ በተሰማሩ ባለሞያዎች የስነ ምግባር ችግር የሚፈጠሩ የተደራሽነት ችግሮች አይኖሩም ማለት አይደለም፡፡ የእነዚህ ችግሮች መገለጫ ከሚሆኑ ምክንያቶች ውስጥ፤በስራ ጊዜ በስራ ገበታ ላይ አለመገኘት፣ተገቢ ያልሆነ ቀጠሮ መስጠት፣በሙስና ምክንያት አንድኛውን ወገን አግኝቶ ሌላውን ወገን እኩል እድል አለመስጠት፣ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የስነምግባር መርሆዎችን ስንመለከት፤እንዴት አድርጎ በፍትህ ስርአቱ ውስጥ ተደራሽነትን ማስፈን እንደሚቻልና የተደራሽነት ችግር በፍትህ ስርአቱና በአጠቃላይ በፍትህ ላይ ምን አይነት አደጋን እንደሚጋብዝ መለየት እንችላለን፡፡

የፍትህ ስርአቱን ዉጤታማ፣ተገማችና ተደራሽ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎችን መስራት ይገባል፡፡ ከነዚህ ስራዎች አንዱና ዋንኛው በስርአቱ ውስጥ ተሰማርተው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙትን ባለሞያዎች በሙያ ስነምግባር ማነጽ ነው፡፡ የስነምግባር መርሆዎች እንደየ ሀገሩና እንደየ ተቋሙ ባህርይ አቀራረጻቸው ሊለያይ ይችላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የስነምግባር መርሆችን በሚመለከት በተወሰኑና ወሳኝ በሆኑ ነጥቦች ላይ በማተኮር ጉዳዩን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን፡፡

(ሀ) *ታማኝነት* (Loyality)- በሁሉም የሙያ መስክ ታማኝነት ዋና መርህ ነው፡፡ የሙያን ክንውን ከታማኝነት ውጭ አድርጎ መመልከት በሙያው በመጨረሻ የሚጠበቀውን ውጤት ዋጋ ማሳጣት ነው የሚሆነው፡፡ በወንጀልም ሆነ በፍትሀ ብሄር የፍትህ አስተዳደር በሚካሔድ ክርክር የሚሳተፉ ወገኖች የሁሉም ታማኝነት የሚገለጽባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ በአንዳንድ ክርክሮች ግለሰቦች በራሳቸው የሚከራከሩበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በዚህ ደረጃ እየተነጋገርን ያለነው ስለ ሙያ ስነምግባር በመሆኑ ትኩረታችን የሚሆነው በዳኞች፣በጠበቆችና በአቃቤያነህግ ላይ ይሆናል፡፡

በወንጀልም ሆነ በፍትሀ ብሄር የፍትህ አስተዳደር የክርክር ሂደት ስራቸውን ከሚያከናውኑ አካላት ዋነኞቹ ዳኞች ናቸው፡፡ ዳኞች በክርክሩ ሂደት ክርክሩን በመምራትና ምስክሮችን በመመርመር ይሳተፋሉ፡፡ ዳኞች ክርክሩን ለመምራትና ማስረጃዎችን ለመመርመር ስራቸውን በሚገባ ለማከናወን በስነምግባራቸው ታማኝ ሆነው መገኘት አለባቸው፡፡ ዳኞች ታማኝ መሆን ያለባቸው ለሚያገለግሉት ህብረተሰብ፣ለህግና ለሞያቸው ነው፡፡ የሾማቸውንና አደራ የሰጣቸውን ህዝብ ከሚያሳዝን፣ከህግ ውጭ የሆነ ስራ ከመስራትና ከሞያቸው መሰረታዊ መርህ በማፈንገጥ ተገቢ ያልሆነ አቅጣጫ ከመያዝ በመቆጠብ ሀላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ታማኝነታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ዳኞች በዚህ መልኩ ታማኝነታቸውን መወጣት ከቻሉ፤ የሚከናወነው የፍርድ ሂደት ተገማች፣ተደራሽና ውጤታማ እንዲሆን አርአያነት ያለው ተግባር መፈጸም ይችላሉ፡፡

በአንድ የፍትህ አስተዳደር የክርክር ሂደት ተገቢ ስፍራ የሚይዙት ተከራካሪ ወገኖች ናቸው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ተከራካሪ ወገኖች ስንል ጠበቆች ወይንም ተከላካይ ጠበቆችና አቃቤያነህግን ማለታችን ነው፡፡ ጠበቆችና አቃቤያነህግ በክርክሩ ሂደት ታማኝ ሆነው ስራቸውን በማከናወን ለፍርዱ ሂደት ውጤታማነት፣ተገማችነትና ተደራሽነት የየራሳቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡ ጠበቆች ታማኝ መሆን ያለባቸው ለሞያቸው፣ለህግ፣ለደንበኞቻቸውና ለሌላው ተከራካሪ ወገን ነው፡፡ ለህግ ታማኝ በመሆን የክርክሩ ሂደት በህግ መሰረት (due process) እንዲከናወን የራሳቸውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተገቢ ያልሆነ ክርክርና ማስረጃ ባለማቅረብ ደግሞ ለፍርዱ ሂደትና ለሌላው ተከራካሪ ወገን ታማኝ መሆን አለባቸው፡፡ ከራሳቸው ደንበኞች ጋር ያላቸው ግንኙነት መመስረት ያለበት በታማኝነት ላይ መሆን አለበት፡፡

አቃቤያነህግ ተከራካሪ ወገን ሆነው ይቀርባሉ፡፡ ምንም እንኳ የወንጀል ተበዳዮችን ጉዳይ በመያዝ ለክርክር ቢቀርቡም ሃላፊነታቸው ግን የህግንና የፍትህን ጉዳይ በተመከተ የተከሳሽ የሆነው ጉዳይም ይመለከታቸዋል፡፡ የአቃቤ ህግ ታማኝነትን ስንመለከት ከዳኞች ጋር

በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚያገለግሉት ህብረተሰብ፣ለሞያቸውና ለህግ ታማኝ መሆን አለባቸው፡፡ ስራቸውንም በዚህ መልኩ በማከናወን ለፍርዱ ሂደት ውጤታማነት፣ተገማችነትና ተደራሽነት የራሳቸውን ሀላፊነት መወጣት አለባቸው፡፡

**(ለ) ገለልተኝነት** (impartial)- ብዙ ጊዜ ስለገለልተኝነት ሲነሳ ወደአእምሯችን ቶሎ የሚመጣው ገለልተኛ ዳኝነት ነው፡፡ ስለሙያ ስነምግባር ስንነጋገር ግን ገለልተኝነት ለሁሉም የሞያ ዘርፍ አስፈላጊ እንደሆን እንረዳለን፡፡ ሁሉም ባለሞያዎች ህብረተሰቡን በእኩል ለማገልገል ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ሁሉንም የህብረተሰብ አባል በእኩልነት ለማገልገል ደግሞ እራሳቸውን ከማናቸውም ወገን ገለልተኛ አድርገው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ዳኞች በወንጀልም ሆነ በፍትሀ ብሄር የፍትህ አስተዳደር የክርክር ሂደት ክርክሩን የመምራት ሀላፊነት አለባቸው፡፡ በፊታቸው ቀርበው የሚከራከሩ ወገኖችንም እኩል በመመልከት ክርክራቸውንና ማስረጃቸውን መስማት አለባቸው፡፡ ዳኞች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ውሳኔው አንድኛውን ወገን ማስደሰቱ፤ሌላውን ወገን ደግሞ ማሳዘኑ አይቀርም፡፡ ክርክሩ ከተጠናቀቀ በኂላ ዳኞች የትኛው ወገን በተሸለ አስረደቷል የሚለውን በመያዝ ውሳኔ የሚሰጡ በመሆናቸው፤በዚህ ደረጃ ገለልተኛ የሆነ ውሳኔ እንዲሰጡ አይጠበቅም፡፡ ዳኞች ገለልተኛ ሆነው ስራቸውን እንዲያከናውኑ የሚጠበቀው ሁለቱንም ወገኖች በእኩል በመመልከትና እኩል እድል በመስጠት ክርክራቸውን እንዲያስረዱ በማድረግ ነው፡፡

ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ክርክር ይዘወ የሚቀርቡና የሚከራከሩ በመሆናቸው በመሆናቸው፤በምን መልኩ ገለልተኛ መሆን እንዳለባቸው ግራ ሊያጋባ ይችላል፡፡ የተከራካሪ ወገኖች ገለልተኝነትን በሚመለከት ለምሳሌ የመክፈቻ ንግግር በመያቀርቡበት ጊዜ ገለልተኛ ሆነው ማቅረብ እንዳለባቸው በህግ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ክርክር ወደ ሌላው ሂደት ለመሸጋገር ፍርድ ቤቱ ብይን ወይንም ትእዛዝ መስጠት የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ብይን ወይም ትእዛዝ በቂ ምክንያት

ከሌላቸው በስተቀር የእኔን ክርክር በሚነካ መልኩ ትእዛዝ ተሰጥቷል በመል ምክንያት ብቻ መቃወም የለባቸውም። እንደዚህ አይነት ትክክለኛ ትእዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ገለልተኛ ሆኖ መቀበል ያስፈልጋል።

(ሐ) **የሞያ ብቃት** (competence) - የሞያ ብቃት በማናቸውም ዘርፍ ለሚቀመጥ የስነምግባር መርህ ዋነኛውን ስፍራ ይዞ የገኛል። በዚህ ደረጃ የሚታይ ችግር በሌሎች የስነምግባር መርሆች የሚሸፈን ባለመሆኑ በዘርፉ የጻፉ ምሁራን ተገቢ ጥንቃቄ እንዲደረግ ይመክራሉ። የሞያ ብቃት በአንድ ወቅት በሚደረግ የትምህርት ምረቃ ተረጋግጦ የሚቆም ሳይሆን በየጊዜው በንባብና በስልጠና መደገፍ ይኖርበታል። ስለዚህ የሞያ ብቃት ሲባል በሙያው የተሰማሩ ባለሞያዎች ያላቸውን የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ብቻ የሚመለከት ሳይሆን፤አሁን ባሉበት ሁኔታ ስራቸውን በአገባቡና በትክክል ለመስራት የሚያስችል እርግጠኛ እውቀት አላቸው ወይ የሚለውንም የሚያጠቃልል ነው።

አለማችን ፈጣንና ተለዋዋጭ በሆነ ሂደት ላይ የምትጓዘው በመሆኗ፤ ትናንት የነበሩ ጽንሰ-ሀሳቦችና ንድፈ-ሀሳቦች በዚሁ መልኩ የተለወጠን ሁኔታ ሊይዙ ይችላሉ። እንደዚህ አይነቱ ክፍተት መሙላት የሚቻለው ደግሞ ወቅታዊ ጽሁፎችን በማንበብና ተገቢ ስልጠናዎችን በመውሰድ ነው። በፌደራልና በክልል ደረጃ የፍትህ አካላት ባለሞያዎች ስልጠና ማእከላትን ማቋቋም ያስፈለገበትም አንድኛው ምክንያት ይኸው ነው።

በህግ ሞያ ከፍተኛ ችሎታችንን የምናሳይበት አንዱ ቦታ ክርክር ነው። ወደፊት በስፋት እንደምንመለከተው የክርክር ክህሎት ቀልጣፋና በሳል አእምሮን የሚጠይቅ ነው። የበሰለና ቀልጣፋ አእምሮ እንዲኖር ደግሞ እራስን ብቁ ለማድረግ የሚያስችልን ማንኛውንም እንቅስቃሴ ለማድረግ እራስን ማዘጋጀትና ከጊዜው ጋር ከሚመጡ እድገቶች እራስን ማስማማት ያስፈልጋል። ትናንት የጨበጥናቸው እውቀቶች በአስተማማኝ ሊረዱንና ልንጠቀምባቸው የምችለው ያሉባቸውን ክፍተቶች በመሙላት ምሉእ ስናደርጋቸው ነው።

(መ) **የተሟላ ስብእና** (integrity) - የቃሉን የእንግሊዝኛ ቃል አንዳንድ ቦታ ላይ ቅንነት በሚለው የአማርኛ ቃል ተተርጉሞ እናገኘዋለን፡፡ የዳኝነት ስነምግባር መርሆችን በአዘጋጀው የቤንጋሎር ሰነድ ላይ እንደተመለከተው ደግሞ ቃሉ ቅንነትን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ሌሎችንም መልካም ግለ ባህርያትንም የሚያጠቃልል ሆኖ ይታያል፡፡ በዚህ ጽሁፍ የተሟላ ስብእና የሚለው ቅንነትን፣አለባበስና ንጽህናን፣ሰአት አክባሪነትን፣ወጥነትን (consistant) ፣ ወ.ዘ.ተ. አጠቃሎ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

በማንኛውም እንቅስቃሴ ሰዎች ከሰዎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ነገራቸው የሰመረና የተስተካከለ ሆኖ እንዲገኝ አንዳቸው ለአንዳቸው ቅን ሆነው መገኘት አለባቸው፡፡ ሰዎች ውል ሲያደርጉ፣የሚተዳደሩበትን የህግ ሰነድ ሲያዘጋጁ፤የፖለቲካ ውይይት ሲያደርጉ፣ማህበራዊ ግንኙነቶችን ሲፈጽሙ፣ወ.ዘ.ተ. በቀና ልቦና ካላከናወኑት በስተቀር ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

በፍትህ አስተዳደር የክርክር ሂደትም ሰዎች ስራቸውን በቀናነት እንዲያከናውኑ የሚፈለገው፤ከዚህ ውጭ የሆነው አካሄድ ትክክለኛ ፍትህን ለማስፈንና ትክክለኛ መደምደሚያ ላይ ለማድረስ ስለማያስችል ነው፡፡ ሰዎች በፍርድ ቤት የሚከራከሩት ለማሸነፍ ቢሆንም፤ ውጤቱ መምጣት ያለበት ትክክለኛ ፍትህን በማስፈን መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ ክርክሮች በቀናነት እንዲካሄዱ ማንኛውም በክርክሩ ሂደት ተሳታፊ የሆነ ወገን የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡ ከዚህ በስተቀር ኢንተግሪቲ የሚለው ቃል ሌሎች ሀሳቦችንም የሚያካትት ቢሆንም ለአሁኑ ቅንነት በሚለው በመወሰን ማጠቃለል ተገቢ ነው፡፡

ስለስነምግባር መርሆዎች ስንነጋገር ሌሎች ነጥቦችም እንዳሉ ማስተዋል ይገባል፡፡ የዚህ ጽሁፍ አላማ ሰለስነምግባር በስፋት ለመነጋገር ሳይሆን በክርክር ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የባህሪ መለኪያዎችን ማስቀመጥ ነው፡፡ ዳኞች፣አቃቤያነህግና ጠበቆች የየራሳቸው የስነምግባር መመሪያ ስላላቸው፤ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች በቂ ናቸው፡፡

# ሦስት

## ለፍርድ ሂደት መዘጋጀት

በወንጀልም ሆነ በፍትሀብሄር የፍትህ አስተዳደር ለፍርድ ሂደት የሚደረግ ዝግጅት (trial preparation) በክርክሩ ውጤት ላይ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፍርድ ሂደት ዝግጅት በጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር (case flow management) ላይ ተገቢ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ከዚህም አንጻር የፍርድ ሂደት ዝግጅት ለተከራካሪ ወገኖች ብቻ የሚተው ሳይሆን በሂደቱ የሚሳተፉ ሁሉ ተግባር ነው፡፡ በሀገራችን የክርክር ስርአት በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢ ትኩረት ባለመሰጠቱ፤ ባለፉት ጊዚያት የፍትህ ስርአታችንን ውጤታማነት እና ቀልጣፋነት ከሚፈታተኑ ተግዳሮቶች አንዱ ሆኖ ይስተዋል ነበር፡፡ በአሁኑ ሰአት አበራታች ሁኔታዎች ቢኖሩም፤ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተቀርፏል ለማለት ግን አይቻልም፡፡ በመሆኑም በዚህ እረገድ የሚሰጠው ስልጠና ችግሩን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

የፍርድ ሂደት ዝግጅት ለወንጀልም ሆነ ለፍትሃብሄር ክርከሮች አስፈላጊ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ በዚህ ዙርያ የሚቀርቡ ጽሁፎች ትኩረታቸው በወንጀል ጉዳዮች ላይ ያጋደሉ በመሆናቸው ተገቢ ያልሆነ ግንዛቤ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ከላይ በክፍል አንድ የክርክር ክህሎትን በሚመለከት የፍርድ ሂደት የሚያካትተው የከሳሽ ክስ እና የተከሳሽ መልስ ከተከናወነ በኂላ ያለውን ሂደት ነው፡፡ የፍርድ ሂደት ዝግጅት ተከሳሽ መልስ ከሰጠ በኂላ እና ከሳሽ/ተከሳሽ ማስረጃ ከማሰማቱ በፊት ያለውን የፍርድ ሂደት የሚመለከት በመሆኑ፤ጉዳዩን በዚህ መልኩ ልንመለከተው ይገባል፡፡ በፍርድ ሂደት ዝግጅት በርካታ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ እነዚህንም ተግባራት እንደሚከተለው አንድ በአንድ እንመለከታለን፡፡

(1)<u>መዝገብንና ማስረጃን መመርመር</u>- በከሳሽነትም ሆነ በተከሳሽነት ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚከራከር ሰው ወይም አካል ስለሚከራከርበት ጉዳይ መዝገብ ይኖረዋል፡፡ በመዝገቡ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ ምክንያቶች የተለያዩ ሰነዶች መቀመጥ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሰነዶች በክርክር ከተያዘው ጉዳይ ጋር ሊኖራቸው የሚችለውን አግባብነት መወሰን የሚቻለው መዝገቡን በመመርመር ነው፡፡ መዝገቡን በምንመረምርበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው በውስጡ ያሉት ሰነዶች በክርከሩ መጨረሻ ለሚጠበቀው ውጤት ምን ፋይዳ አላቸው የሚለው መረ አስተሳሰብ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ መዝገብን በአግባቡ ባለመመርመር ሰነዶች ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ልንጠቀምባቸው ወይንም ሳንጠቀምባቸው ልንቀር አንችላለን፡፡ ይህም በክርክሩ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ሁለት ጉዳዮች ብንመለከት መዝገብን ባለመመርመር ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ሁኔታ መገንዘብ ይቻልል፡፡

የመጀመርያውን ጉዳይ በተመለከተ ጸሀፊው ነገሩን ለመከታተል የቻለው በ1987ዓ/ም ሰሜን ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ዐቃቤ ህግ በተከሳቹ ላይ በመሰረተው ክስ ተከሳሾች (በቁጥር አራት ሰዎች) በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 32-1-ሀ-523 ( በአሁኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 540 ) የተመለከተውን በመተላለፍ ሟቹን በድንጋይ እና በዱላ በመምታት ስለገደሉት በፈጸሙት ወንጀል ተከሰዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተከሳሾች በሰጡት እምነት ክህደት ቃል ጥፋተኞች አይደለንም በማለታቸው ዐቃቤ ህግ ሶስት ምስክሮችንና ስለሟች ሞት ምክንያት የሚገልጽ የህክምና ማስረጃ አቅረቧል፡፡ በዚሁ የዐቃቤ ህግ ማሰረጃ ተጠቃሏል፡፡ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ሲመረምር የተሰሙት ምስክሮች አንድ በሆነ ቃል ተከሳሾቹ በሟች የተለያዩ አካላት በዱላና በድንጋይ በመምታት እንደገደሉት አስረድተዋል፡፡ የቀረበው የህክምና ማስረጃ ሟች ሊሞት የቻለው በግንባሩ ላይ በሹል ነገር ተወግቶ እንደሆነና በሌላዉ የሰውነት አካሉ ላይ የደረሰበት ምንም አይነት ጉዳት እንደሌለ ይገልጻል፡፡ በዐቃቤ ህግ የሰው እና የህክምና ማስረጃ

መካከል የሚታየው ክፍተት ሰፊ ጥርጣሬን የሚፈጥር በመሆኑ ተከሳሾቹ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነፃ ተሰናብተዋል፡፡

በዚህ መዝገብ ላይ የተፈጠረውን ሁኔታ ስንመለከት መዝገብን በመመርመር ደረጃ ምንም ስራ አለመሰራቱን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ ተገቢ ስራ ተሰርቶ ቢሆን ኖሮ የምስሮቹ ቃል ከህክምናው ማስረጃው ጋር በትክክል ተጣጥሞ እንዲቀርብ ማድረግ በተቻለ ነበር፡፡

ሁለተኛው ጉዳይ በ1993 ዓ/ም ካናቢስ የተባለ አደንዛዥ ዕጽ ይዘው በተገኙ አንድ መነኩሴ ላይ የቀረበ ክስ ነበር፡፡ ተከሳሹ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመከራከራቸው ዐቃቤ ህግ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ቁጥር 35 መሰረት የሰጡት ቃል እና በተያዘው ዕጽ ላይ የተደረገው የላቦራቶር ምርመራ ውጤት ነው፡፡ ተከሳሹ በምርመራ ወቅት ለፍርድ ቤት በሰጡት ቃል ዕጹ ለዘወትር እጸፋሪስ ተብሎ እንደሚ ጠራና ከጥንት ጀምሮ ለመንፈሳዊ ተማሪዎች ለመድሀኒትነት አገልግሎት የሚውል በመሆኑ በመንግስት ሊወረስ አይገባም የሚል ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ወንወጀል የሚያስቀጣው ሆን ተብሎ ሲፈጸም ነው፡፡ የቀረበው ማስረጃ ግን የተከሳሹን ወንጀል የመስራት ሀሳብ አያመለክትም፡፡ በተቃራኒው ማስረጃው የሚገልጸው ተከሳሹ እፁን የያዙት በቅን ልቦና ለበጎ ተግባር አውለዋለሁ በሚል ሀሳብ እንደሆነ ነው፡፡

ባልተሟላ የክስ ሂደት ዝግጅት ማንኛውም ተከራክሪ ወገን ሊገጥመው የሚችለው ችግር ምን ሊሆን እንደሚችል ከላይ ለአብነት የተጠቀሱት ጉዳዮች በቂ ማረጋገጫ ናቸው፡፡ መዝገብንና ማስረጃን በመመርመር የሚደረግ ዝግጅት የክርክሩ ሂደት የተስተካከለ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ፤በፍርድ ውጤትም ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ የኖረዋል፡፡

(2) <u>የጉዳይ ፅንሰ ሀሳብ ማዳበር</u> (Develop case theory) አንድ ጉዳይ በመጀመርያ ሲቀርብ ባልተያያዘና በተበታተነ መልኩ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይህም ነገሩን በቀላሉ ለመረዳትና

ለማስረዳት እንዳይቻል ሊያደርግ ይችላል፡፡ አንድ ድርሰት መግቢያ፣ ሀተታና መደምደሚያ እንዳለው፤የጉዳይንም ፍሰት ስርአት በአለው ሁኔታ ለመረዳትና ለማስረዳት ጉዳዩን በሚገባ ማደራጀት ይገባል፡፡ በሚገባ ያልተያያዘና ያልተደራጀ ጉዳይንና አስተሳሰብን በክርክር ሂደት የተደነቃቀፈና የተወለጋገደ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ እንኳን ክርክርን ያህል ትልቅ ጉዳይ ይቅርና በማናቸውም ጊዜ ሃሳብን ለማቅረብ ሲሞከር፤ያልተቀነባበረና ያልተደራጀ አስተያየት ሰወችን ግምት ውስጥ ሊጥል ይችላል፡፡ ሀሳብን አስተካክሎና አሳክቶ ማቅረብ የሚቻለው የሚኖረንን አስተሳሰብ ስናደራጀው ብቻ ነው፡፡

በአንድ ክርክር የሚነሱ ጭብጦችና የሚቀርቡ ማስረጃዎች በቅደም ተከተል ቢቀመጡ ለአቅራቢውም ሆነ ለሚቀርብለት ወገን አመች ይሆናል፡፡ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅድም ተከተል ለመለየትና የነገሩን አመጣጥ ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ ተያያዥነት ባለው መልኩ የምናደራጅበት ስራ የጉዳይን ፅንሰ ሀሳብ ማዳበር በማለት እንለየዋለን፡፡ ምስክሮችን በምንሰማበት ጊዜ በቅደም ተከተል መሆን አለበት፡፡ ምስክሮች አንድ ላይ ባሉበት ሁኔታ መስማት አይቻልም፡፡ በቅደም ተከተል መሰማት አለባቸው፡፡ እዚህ ላይ ግን ቅደም ተከተል ሲባል ይህን አይነቱን ቅደም ተከተል አይደለም፡፡ ቅደም ተከተል ስንል ካዳበርነው የጉዳይ ፅንሰ ሀሳብ አንጻር የትኛው ምስክር ከየትኛው መቅደም አለበት፤የትኛው ምስክር በመጨረሻ መሰማት አለበት ማለት ነው፡፡

ጭብጦች በባህርያቸው ያንደኛው ጭብጥ ውጤት ለሌለኛው ጭብጥ በግብአትነት የሚያገለግል በመሆኑ፤ጭብጦቹን ለማስረዳት የምናቀርባቸው ማስረጃዎችም የጭብጦቹን ቅደም ተከተል ፍሰት ተከትለው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ የጉዳያችንን ፅንሰ ሀሳብ ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን የያዘውን ጉዳይ በሚገባ ለመረዳት፣ ለሌሎች ለማስረዳት፣በትክክለኛ ሁኔታ ለማቅረብ፣በአግባቡ ለመከታተል እና ሂደቱን ለመቆጣጠር እንዲችል የጉዳዩን ፅንሰ ሀሳብ ማዳበር ይኖርበታል፡፡

የጉዳይ ጽንሰ ሀሳብ ማዳበር የህግና የፍሬ ነገር በመለየት በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ ህግን በሚመለከት ጽንሰ ሀሳቡ የክርክሩ የህግ ውጤት ምን እንደሚሆን በሚገባ የሚያመላክት መሆን አለበት፡፡ ፍሬ ነገርን በሚመለከት የምናዘጋጀው ጽንሰ ሀሳብ ከምናቀርበው ማስረጃ ክብደት ጋር የሚጣጣም ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

(3) <u>የሌላውን ክርክር መገመት</u> (Anticipate possible defense) በክርክር ሂደት ተከራካሪ የሆነ ወገን ስለእራሱ በሚያውቀው ብቻ ሳይሆን ሌላውም ተከራካሪ ወገን ሊያነሳው በሚችለው ነጥብም ላይ ተገቢ ዝግጅት ማድረግ አለበት፡፡ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ሊያነሳቸው የሚችላቸውን የክርክር ነጥቦች ሁሉንም በትክክል ማወቅ ሊያዳግት ይችላል፡፡ ነገር ግን ከክርክሩ ባህሪ አንጻር ምን ዓይነቶች ጉዳዮች መነሳት እንደሚገባቸው መገመት አያዳግትም፡፡ ክርክሩን ለማስረዳት ምስክር የቀረበ ተከራካሪ ወገን ዋናውን ጥያቄ በሚጠይቅበት ጊዜ በአዕምሮው ላይ ሊያስቀምጠው የሚገባው ነገር ሌላው ተከራካሪ ወገን ሊያቀርበው የሚችለው መስቀልኛ ጥያቅ ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን ሀሳብ ነው፡፡ እንደዚህ በማሰብ የሚደረግ እንቅስቃሴ የራስን አቋም የሚያጠናክር ሲሆን፤በሌላ በኩል የሌላውን ወገን የክርክር ዕድል በማጥበብ ተገቢ ለሆነ ውጤት ያበቃል፡፡

ለምሳሌ የአስገድዶ መድፈርን የወንጀል ድርጊት እንመልከት፤ይህ የወንጀል ድርጊት ሲፈጸም ሁለት ነጥቦች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ሁለቱንም ነጠቦች በበቂ ሁኔታ ማስረዳት ይገባል፡፡ ድርጊቱን የፈጸመው ተከሳሹ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ተከሳሹ ድርጊቱን የፈጸመው በማስገድድ እንደሆነ ማስረዳት ይገባል፡፡ ከሳሹ ማስረጃ አቅርቦ ሲያስረዳ በተከሳሹ በኩል ሊነሳ የሚችለው መስቀልኛ ጥያቄ ወይም መከላከያ ድረጊቱን የፈጸምኩት እኔ አይደለሁም ወይንም ድርጊቱን የፈጸምኩት በግል ተበዳይ ፈቃድ ነው የሚል እንደሚሆን በሚገባ መገመት አለበት፡፡ በመሆኑም በሚያቀርበው ዋና ጥያቄና ማስረጃ በተከሳሹ ማንነት እና በግል ተበዳይ የፈቃድ ጉድለት ላይ ለመስቀልኛ ጥያቄ በር የሚከፍቱ ሁኔታወችን በር መዝጋት አለበት፡፡

(4) <u>ምስክሮችን ማግኘት እና ማዘጋጀት</u> - በወንጀልም ሆነ በፍትሀ ብሄር ክርክር በዋነኝነት ከሚቀርቡ ማስረጃዎች አንዱ የሰው ምስክርነት ነው፡፡ ምስክሮች የተፈጸመውን ድርጊት የተረዱበት እና ቀርበው ለፍርድ ቤት ቃል የሚሰጡበት ጊዜ ሊለያይ ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ በምስክሮቹ አስረጅነት ላይ አሉታዊ ተጽዕና ሊያሳድር ይችላል፡፡ በሌላም በኩል ነገሩ ከምስክሮች ማስተዋስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከምስክሮቹም ማንነት ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡ ምስክሮቹ ልዩ ትኩረት የሚሹ (vulnerable) ወይንም ፍርድ ቤት በመቅረባቸው ፍርሀት የሚያድርባቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በነዚህም ምክንያቶች ምስክሮቹን አስቀድሞ ማግኘትና ማዘጋጀት ሊያስፈልግ ግድ ይላል፡፡

ምስክሮችን ማግኘት እና ማዘጋጀት ሲባል ምስክሮችን መምከርና ማሳመን ማለት አይደለም፡፡ ምስክሮችን ማግኘትና ማዘጋጀት ማለት ምክሮቹ አስቀድመው የሚያውቁትን ጉዳይ አስታውሰውና አስተውለው የለፍርሀትና ያለጭንቀት ትክክለኛውን ነገር ለፍርድ ቤት እንዲያስረዱ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ከዚህም አንጻር ምስክሮችን በምናገኝበትና በምናዘጋጅበት ጊዜ ተገቢ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡ አካሄዳችን መሰረታዊ በሆኑ መርሆዎች ላይ መመስረት ስላለበት የሚተሉትን ነጥቦች በመከተል መስራት ይጠበቅብናል፡፡

- ለምስክሮች ቃለ-መጠይቅ ማዘገዘጀት እና ቃለ-መጠይቁን በጥንቃቄ ማድረግ፡፡
- ቃለ-መጠይቅ በሚደረግበት ጊዜ መሪ ጥያቄ ከመጠየቅና አስተያየት ከመስጠት መቆጠብ (without leading and suggestion)
- ፍርሀት የሚያድርባቸው ወይም ልዩ ትኩረት የሚሹ ምስክሮች ከሆኑ፤ ጭንቀታቸው እና ፍርሀታቸው እንዲቀንስላቸው ቃላቸውን የሚሰጡበትን ቦታ ማሳየት፡፡
- ለምስክሮች የዳኛውን፣የጠበቃውነ እና የዐቃቤ ህጉን ሚና ማስረዳት፡፡
- የዋናን ጥያቄና የመስቀልኛ ጥያቄን ሂደት ለምስክሮቹ ማስረዳት፡፡

. በችሎት የሚቀመጠው ዳኛ ስለሚሰጡት ምስክርነት ምንም የሚያውቀው

ነገር እንደሌለና ስለጉዳዩ ከእነሱ እንደሚረዳ ለምስክሮቹ መግለጽ፡፡

. በዋና ጥየቄ መሪ ጥያቄ እንደማይጠየቁን በመስቀልኛ ጥያቄ ጊዜ ግን

እንደሚጠየቁ መንገር፡፡

የፍርድ ሂደት ዝግጅት ክርክርን በአጥጋቢ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው በመሆኑ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው፡፡ በተግባር እንደሚስተዋለው በዚህ እረገድ ያለው እንቅስቃሴ ግን በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡

<u>መልመጃ</u>

(1) እርስዎ ዐቃቤህግ ወይም ጠበቃ ሆነው በሚከራከሩበት ጉዳይ የሚያስረዱለወትን ምስክሮች አስቀድሞው በማገኘት ያዘጋጇቸዋል ወይ? በሚያዘጋጇቸውሰ ጊዜ በምን መልኩ ነው የሚያዘጋጇቸው? ካላዘጋጇቸውሰ ምክንያቱ ምንድን ነው? በነዚህ ጉዳዮች ላይ ከቡድንዎ አባሎች ጋር ይወያዩባቸው፡፡

(2) ዳኛ ወይንም ዐቃቤህግ በመሆን በሰሩባቸው ግዚያት ችሎት ከመቅረብዎ በፊት በያዙት መዝገብ ላይ ተገቢ ዝግጅት ባለማድረግዎ ያጋጠመዎት ሁኔታ ካለ እስቲ ከቡድንዎ አባሎች ጋር በመነጋገር እርስ በርሳችሁ የተሞክሮ ልውውጥ ለማድረግ የሞክሩ፡፡

(3) በተግባር አንዳንድ ጊዜ ዐቃቤህግ ምስክሮቹን ችሎት ከመጀመሩ በፊት በጽህፈት ቤት አስጠርቶ በሚያነጋግርበት ሰአት ድርጊቱን በመቃዎም ለችሎት አቤቱታ ይቀርባል፡፡ ለእንደዚህ ላለው ተቃውሞ ምክንያት ተደረጎ የሚቀርበው ነጥብ ምንድን ነው? ተቃውሞውስ አግባብነት አለው ወይ?

(4) የቡድን አባሎች በትክክል በተግባር በአለው አፈጻጸም ላይ በመነጋገር እና ያሉትን ችግሮች በመለየት መደረግ ስለአለበት ሁኔታ ይወያዩበት፡፡

## አራት

## የመክፈቻ ንግግር (opening statement)

የፍርድ ሂደት ከሚያካትታቸው አብይ ጉዳዮች አንዱ የመክፈቻ ንግግር ነው፡፡ የወንጀልም ሆነ በፍትሀብሄር የፍትህ አስተዳደር ስርአት የክርክር ሂደት የሚጀመረው በዚህ የሰራ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በሀገራችን በወንጀለኛ ስነ-ስርአት ህግና በፍትህ ብሄር ስነ-ስርአት ህግ እንደ ቅደም ተከተሉ በአንቀጽ 136 እና 258 ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የመክፈቻ ንግግር የሚደረገው ለክርክሩ መልስ ከተሰጠ በኋላና ማስረጃ ከመሰምቱ በፊት ነው፡፡ በመሆኑም የመክፈቻ ንግግር ስለክሱ፣ ስለመልሱ አና ስለሚቀርበው ማስረጃ የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የከሳሽ ክርክርና ማስረጃ ከተጠናቀቀ በኋላ ተከሳሹ የቀረበበትን ክስና ማስረጃ መከላከል የሚያስፈልገው ከሆነ ስለመከላከያው የመክፈቻ ንግግር አያደርግም ማለት አይደለም፡፡

የመክፈቻ ንግግር ስለቀረበ ክስና ስለሚቀርብ ማስረጃ የሚገልጽ በመሆኑ፤ዳኞችን ወይም ተከራካሪውን ወገን ለማሳመን የሚቀርብ ክርክር አይደለም፡፡ ዳኞች በጉዳዩ ላይ አስተያየት መስጠት የሚችሉት ክርክሩና ማስረጃው ከተጠናቀቀ እና ተገቢውን ግንዛቤ ከጨበጡ በኋላ በመሆኑ፤ማስረጃ ከመቅረቡ በፊት ዳኞችን ለማሳመን የሚቀርብ ክርክር አግባብነት የለውም፡፡ በእርግጥ የመክፈቻ ንግግር ክርክርና ማስረጃን በማያያዝ የሚቀርብ በመሆኑ የማሳመን ዝንባሌ አይኖረውም ማለት እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ዋናው አላማው ግን ስለክርክሩ የሚቀርበውን ማስረጃ በተመለከተ ለዳኞች ተገቢውን ግንዛቤ ለማስያዝ በመሆኑ፤የራስን በማጉላትና የሌላውን ዝቅ በማድረግ መልኩ የሚቀርብ ክርክር አይደለም፡፡

መልካም አፈጻጸም የመልካም ጅማሮ ውጤት ነው፡፡ በፍረድ ሂደት የሚቀርብ ክርክር ውጤትም፣ ክርክሩ ሲጀመር በሚቀርበው የመክፈቻ ንግግር አቅጣጫ የሚይዝ በመሆኑ፣የመክፈቻ ንግግር ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ የመክፈቻ ንግግር ጉዳዩን ለማስረዳት ስለሚቀርበው ማስረጃ በቂ መረጃ (information) የሚሰጥ በመሆኑና በክርክሩ የሚሳተፉ ወይም የሚከታተሉ ወገኖች በዚሁ ግንዛቤ ላይ ተመርኩዘው የስራቸውን እንቅስቃሴ ስለሚያደርጉ ለክርከሩ የመንገድ ካርታ (Road map) በመሆን ያገለግላል፡፡ በአግባቡ ተደራጅቶ የቀረበ የመክፈቻ ንግግር ጠቃሚነቱ የራስን ክርክር ለማመቻቸት ብቻ ሳይሆን፣ ሌላውም ወገን ጉዳዩን በአግባቡ ተረድቶ እንዲጓዝ ያደርገዋል፡፡ በአንዳንድ ችሎቶች ምስክሮች በሚሰሙበት ጊዜ ሌላው ተከራካሪ ወገን (አንዳንድ ጊዜም ፍርድ ቤት) ለምስክሮቹ ምስክሮቹ በማያስረዱት ጉዳይ ላይ ጥያቄ ሲያቀርቡ ይስተዋላሉ፡፡ ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት ምስክሩን ያቀረበው ወገን በመክፈቻ ንግግሩ ምስክሮቹ ስለሚያስረዱበት ሁኔታ በቂ የሆነ መረጃ ባለመስጠቱ ነው፡፡ (ጸሀፊው የዘር ማጥፋት ወንጀልን የሚመለከተው ችሎት ዳኛ በነበረበት ጊዜ በብዛት እንዳስተዋለው ሰዎች ተገድለው በመንገድ ላይ ተጥለው እንደነበር ለማስረዳት በቀረቡ ምስክሮች ላይ ከሚቀርቡ ጥያቄዎች መካከል ሰዎቹን ማን ነው የገደላቸው የሚል ነው፡፡ ምስክሮቹ የቀረቡት ሟቾቹ በእርግጥ ስለሞሞታቸው ለማስረዳት እንጅ ማን እንደገደላቸው ለማስረዳት አይደለም፡፡ አስቀድሞ በመክፈቻ ንግግር ግን ይህ ጉዳይ በግልጽ ቢቀመጥ ኖሮ እንደዚህ አይነት ጥያቄዎችን በማንሳት ጊዜን ማባከን ባላስፈለገ ነበር፡፡

ይህንን በሚመለከት ጀምስ ደብሊው ጅንስ የተባሉ ጸሀፊ Trial Advocacy በተባለ መጽሀፋቸው በገጽ 305 ላይ ፣The amount of empirical studies which has taken place in the advocycy area has been slim indeed,but some testing has occurred this phase of law suit.It has been discovered that jurors,interviewed after verdict,have confirmed that their ultimate decision corisponding with their

tentative openion after opening statement in over 80 percents of the cases. In othe words convincing them with your opening statement and you have a fuor out of five chance of winning. በማለት የገለጹት ከላይ ለማብራራት እንደተሞከረው የመክፈቻ ንግግር በተለምዶ እንደምናደርገው አስፈላጊነቱ ዝቅ ያለ ሳይሆን በክርክሩ ውጤት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው በስነስርአት ህጎቻችን የክስ መክፈት ስነ-ስርአትን በሚመለከት በአግባቡ ተመልክቷል፡፡ በተግባር የሚታየው አተገባበር ግን ትክክለኛውን ግንዛቤ የያዘ አይመስልም፡፡ በአብዛሀኛውን ጊዜ እንደሚታወቀው በወንጀልም ሆነ በፍትሀ ብሄር የቀረቡት ምስክሮች እንደ ክሱ አመሰራረት የሚያስረዱ በመሆናቸው ይሰሙልን በማለት ከተመዘገበ በኋላ ምስክሮች እንደሚሰሙ ይታወቃል፡፡ ይህ በልምድ የዳበረ ሂደትም ጭብጥ ማስመዝገብ ተብሎ ይታወቃል፡፡ በህጉ ላይ ጭብጥ ማስመዝግብ የሚል ሀሳብ የልም ፡፡ አነጋጋሪ የሚሆነው ይኸ ቃል በህጉ ባለመኖሩ የሚስተዋለው በቅርጽ ላይ ያተኮረው ችግር ብቻ ሳይሆን፤አነጋጋሪ የሚሆነው አተገባበሩ ከህጉ መንፈስ ጋር አብሮ የሚሄድ አለመሆኑ ነው፡፡

ከአንዳንድ ባለሞያወች ለፍርድ ቤቱ ክሱ የደረሰ በመሆኑ የቀረቡት ምስክሮች የሚያስረዱት እንደ ክሱ አመሰራረት ነው መባሉ ምን ችግር አለው የሚል ሀሳብ አለ፡፡ ለምሳሌ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 136 እንደተገለጸው ተከሳሹ የእምነት ክህደት ቃል ከሰጠ በኋላ ዐቃቤ ህግ ክሱን ሲከፍት ሊያስረዳ ያቀረበውን ክስና የሚያቀርበውን ማስረጃ ይገልጻል ይላል፡፡ ተከሳሹ የእምነት ክህደት ቃሉን የሚሰጠው የዐቃቤ ህግ ክስ ከቀረበና ከተነበበለት በኋላ ነው፡፡ ዐቃቤ ህግ ክሱን ሲከፍት ግን የሚያስረዳው ያቀረበውን ክስና የሚያቀርበውን ማስረጃ ነው፡፡ ህጉ ክሱ አንድ ጊዜ ቀርቧልና ክሱ ሲከፈት እንደገና ክሱን ማስረዳት አያስፈልግም አላለም፡፡ የቀረበው ማስረጃ ምንን ለማስረዳት እነደቀረበ ለመግለጽ የግድ ክሱን በድጋሚ ማንሳት ያስፈልጋል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ክስ የመክፈት ስርአት በክርክሩ ለሚሳተፉና ክርክሩን ለሚከታተሉ ወገኖች እንደ ጉዞ ካርታ የሚያገለግል ነው፡፡ ክርክሩን ለማስረዳት የቀረቡ ምስክሮችና ሌሎች ማስረጃዎች በክርክሩ የሚነሱ የተለያዩ ጉዳዮች በተለያየ መልኩ ለማስረዳት የቀረቡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ ባለ ሁኔታ የቀረቡት ምስክሮች ወይንም ማስረጃወች እንደክሱ አመሰራረት የሚያስረዱ በመሆናቸው ይሰሙ ቢባል፤በሌላው ተከራካሪ ወገን ወይም በፍርድ ቤት ምስክሩን የማይመለከቱ ጉዳዮች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም የትኛውን ጉዳይ የትኛው ማስረጃ እንደሚገልጸው ካልታወቀ ሁሉም ማስረጃወች እንደ ክሱ ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ ያስረዳሉ በሚል ግምት የሚያሳስቱ ሁኔታወች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ ምስክር ወይንም ማስረጃ የሚያስረዳው የትኛውን ነጥብ እንደሆነ ካልታወቀ፤ ሁሉንም ነጥቦች ለማስረዳት የቀረበ እንደሆነ ተገምቶ በዚሁ አረዳድ ለመሄድ የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ለዚህም ነው የክስ መክፈቻ ስነስርአት በክርከሩ ውስጥ ላሉ ወገኖች እንደ መንገድ ካርታ ያገለግላል የሚባለው፡፡

## <u>መልመጃ</u>

(1) እርስዎ በዳኝነት ወይንም በተከራካሪነት በሚገኙበት ችሎት በተግባር የሚሰራበትን ከቡድን አባሎች ጋር በመነጋገር ልማዳዊ ከሆነው አሰራር በመውጣት ትክክለኛውን መስመር እንዴት መያዝ እንደሚቻል ሃሳብ ተለዋወጡበት፡፡

(2) በሚደረገው ገለጻና ውይይት ላይ በመመርኮዝ ከጽሁፉ ጋር አባሪ ሆኖ የተያያዘውን የፖሊስ ምርመራ መሰረት በማድረግ በግልዎ የመክፈቻ ንግግር ያዘጋጁ፡፡

(3) ተከሳሽ የዐቃቤህግን ምስክር ወይም ዐቃቤህግ የተከሳሽን ምስክር የመስቀልኛ ጥያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ ምስክሩ ሊያስረዳ ባልተጠራበት ነጥብ ላይ ጥያቄ ሲቀርብ አስተውለው

አያውቁም? በእርስዎ አስተያየት እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ የሚከሰተው በምን ምክንያት ነው ይላሉ?

(4) በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 136 ዐቃቤህጉ ክሱን ሲከፍት ያቀረበውን ክስና ማስረጃ በትክክል እና ያለአድሎ ባጭሩ ይገልጻል ይላል፡፡ በትክክልና ያለአድሎ የሚለው ሃረግ የሚያመለክተው ምንድን ነው?

# አምስት

## ዋና ጥያቄ

ከሳሽ ያቀረበውን ክስ ተከሳሽ በማስተባበል ከተከራከረ ከሳሹ ክሱን ማስረዳት ይጠበቅበታል። ከሳሽ ክሱን ለማስረዳት ከሚያቀርባቸው ማስረጃዎች አንዱ የሰው ምስክርነት ነው። ክሱን ለማስረዳት ለሚቀርቡ ምስክሮች በየደረጃው የተለያዩ ጥያቄዎችን የሚጠየቁ ሲሆን በጠራቸው ወገን የሚቀርብላቸው ጥያቄ ዋና ጥያቄ ይባላል። ምስክሮቹ ያቀረብነው የክስ አቤቱታ ትክክለኛ መሆኑን ያውቁልናለ ተብለው የሚጠሩ በመሆናቸው ጉዳዩን ስለማወቃቸው በጠራቸው ወገን ይጠየቃሉ እንጅ አይመረመሩም።

ስቴቨን ሉቤት የተባሉ ጸሀፊ Modern Trial Advocacy በተባለው መጽሀፋቸው ይህንኑ ጉዳይ በሚገባ ሲያብራሩት፤Examination-in-chief is your opportunity to present the substance of your case.It is the time to offer the evidence that will estabilish the fact you need to prevail. Having planned your persuasive story, you must now prove the fact on which it rest by eliciting the testimony of witnesses. Examination-in-chief,then, is the heart of your case.It is the fulcrum of the trial-the aspect uppon which everything else turns. Every aspect of the trial is derivative of examination-in-chief.በማለት ገልጸውታል።

ዋና ጥያቄን በተመለከተ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 137 እና በፍትሀ-ብሄር ህግ ቁጥር 263 መሰረት ተገልጾ ይገኛል። በሁለቱም ህጎች ላይ እንደተመለከተው በዋና ጥያቄ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ውሳኔ ስለሚሰጥበት ፍሬ ነገር አግባብነት ያላቸው እና ምስክሩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ስለ ጉዳዩ የሚውቃቸውን በሚመለከት ነው።

በመሆኑም ከጉዳዩ ጋር አግባብነት የሌላቸውን ጥየቄዎች ማቅረብ አይቻልም፡፡ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ነጥብ አለ፡፡ ምስክሩ በተዘዋዋሪ ስለሚያውቃቸው ጉዳዮች ማለት ምን ማለት ነው? በተዘዋዋሪ የሚያውቃቸው ነገሮች ምን ምን ሁኔታዎችን ያካትታል? አንዳንድ ባለሞያዎች በተዘዋዋሪ የሚታዎቁ ነገሮች የሚለው የስሚ ስሚን ያካትታል በማለት ሀሰባቸውን ያቀርባሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ምስክሩ በተዘዋዋሪ የሚያውቀው የሚለው የሚመለከተው አካባቢያዊን ማስረጃን ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ ይህንን ነጥብ ያነሳነው በማስረጃ ላይ ከሚቀርቡ መቃወሚያዎች ማስረጃው የስሚ ስሚ በመሆኑ ሊቀርብ አይገባም የሚለው አንዱ በመሆኑ ነው፡፡

የስሚ ስሚ ማስረጃን በተመለከተ በኢትዮጵያ የህግ ስርአት በተግባር እንደሚስተዋለው፤ከተወሰኑ ጉዳዮች በስተቀር የስሚ ስሚ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ለዚህ አስተሳሰብ መሰረቱ( እንደ ጸሀፊው ዕምነት ) በሀገሪቱ በስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙት የህግ ባለሞያዎች የማስረጃን ህግ ትምህረታቸውን ከሚከታተሉበት የመማርያ ጽሁፍ አንዱ እረቂቅ የማስረጃ ህግ በመሆኑ በዚህ ሰነድ የሚገኘው መርህ ነው፡፡ በኮመን ሎው የህግ ስርአት ያሉ አገሮች ከጥቂት ነገሮች በስተቀር የስሚ ስሚ ማስረጃን አይቀበሉም፡፡ እረቂቅ የማስረጃ ህጉም በዚህ የህግ ስርአት መንፈስ የተቀረጸ በመሆኑ አስታሳሰቡ ተቀባይነት እንዲኖረው የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዚህ በስተቀር በማናቸውም የሀገራችን ህጎች የስሚ ስሚ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም የሚል ድንጋጌ የለም፡፡ በተቃራኒው በፍትሃብሄር ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 263 እና በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 137 ምስክሩ በተዘዋዋሪ የሚያውቀው የሚለው ሲተረጎም የስሚ ስሚንም ያጠቃልላል ብሎም ለመከራከር የሚያስችል ይመስላል፡፡ ሆኖም በተግባር እስከ አሁን የተሰራበት ያለውንና የስሚ ስሚ ማስረጃን በሚመለከት አዲስ ህግ ማውጣት ያስፈለገበትን ምክንያት ስንመለከት፤በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት 137 እና በፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ሀግ 263 በተዘዋዋሪ ተብሎ የተገለጸውን

የስሚ ስሚን ያጠቃልላል ብሎ ለመቀበል አከራካሪ ይሆናል፡፡ በአሁኑ ሰአት ግን በኢትዮጵያ የህግ ስርአት ውስጥ ሽብርተኝነትን በሚመለከት ግልጽ በሆነ ድንጋጌ የስሚ ስሚ ማስረጃ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 23 የሽብርተኝነትን ወንጀል ለማስረዳት ከሚቀርቡ ማስረጃዎች አንዱ የስሚ ስሚ ማስረጃ ነው፡፡ ማስረጃ ተቀባይነት አለው ማለት ግን በቂ ነው ማለት አይደለም፡፡በሌላም በኩል ማስረጃም በቂ በመሆኑ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት አይደለም፡፡

ዋና ጥያቄ በሁለት አይነት መንገድ ሊቀርብይችላል፡፡ እነዚህም ክፍት የገለጻ ዘዴ (open narrative method) እና አንድ ባንድ የመጠየቅ ዘዴ(specific question method) ተብለው ይታወቃሉ፡፡ ክፍት የገለጻ ዘዴ የሚባለው ለተወሰኑ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ጠያቂው ጣልቃ ሳይገባ ምስክሩ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያለውን ሁኔታ ለፍርድ ቤት የሚገልጽበት ነው፡፡ አንድ ባንድ የመጠየቅ ዘዴ ደግሞ የምስክሩ መልስ መሰረት የሚያደርገው የጠራው ወገን የሚያቀርበውን ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ማን፣መቼ፣ለምን፣እንዴት፣ወ.ዘ.ተ.የሚሉትን የጥያቄ መነሻ ቃላቶች በመንተራስ ጥያቄ አቅራቢው ምስክሩን ይጠይቃል፡፡ ይህ ማለት ግን ክፍት በሆነ የገለጻ ዘዴ ምስከሩ ቃሉን ሲሰጥ ተመሳሳይ በሆኑ ቃላት ጥያቄ አይቀርብለትም ማለት አይደለም፡፡ አልፎ አልፎም ቢሆን ሊቀርብ ስለሚችል በክልከላ መልክ ሊታይ አይገባም፡፡

በዋና ጥያቄ የሚቀርበው ጥያቄ አማራጭ መልሶችን ለመስጠት የሚያስችል(open ended question) መሆን አለበት፡፡ በመሆኑም መሪ ጥያቄ (leading question) ማቅረብ አይቻልም፡፡ የነገሩ ሁኔታ የግድ የሚል ከሆነ መሪ ጥያቄ በማስፈቀድ ማቅረብ ይቻላል፡፡ በሀገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 137 መሰረት መሪ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ሌላውን ተከራካሪ ወገን በማስፈቀድ ነው፡፡ በሌሎች ሀገሮች ለምሳሌ እንደካናዳ የመሳሰሉትን አገሮች ስንመለከት ግን የሚፈቅደው ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሀገራችን የህግ

ስርአትም ቢሆን ፍርድቤትን በማስፈቀድ መሪ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻልበት ምክንያት አለ፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 44 ላይ እንደተመለከተው ምስክሩ አስጠቂ በሚሆንበት ጊዜ ዐቃቤ ህግ ፍርድ ቤቱን በማስፈቀድ ምስክሩን መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይችላል፡፡ ከዚህ ውጭ ባሉ ምክንያቶች ግን መሪ ጥያቄ ለማቅረብ ፍቃድ የሚጠየቀው ሌላው ተከራካሪ ወገን ነው፡፡

አስጠቂ ምስክርን በሚመለከት አዋጅ ቁጥር 434/1997 ከመውጣቱ በፊት በህግ የተገለጸ ምንም ድንጋጌ አልነበረም፡፡ በህግ የተገለጸ ነገር ባይኖርም በስራ ሂደት ውስጥ ግን ጽንሰ ሀሳቡ አልነበረም ማለት አይደለም፡፡ እንደሚታወቀው የሀገራችን የህግ ስርአት በልምድ የዳበሩ አሰራሮችንም አጣምሮ የያዘ ነው፡፡ ሁሉም ነገር በህግ ብቻ ሊሟላ ስለማይችል፤እንደማንኛውም ሀገር የህግ ስርአት የሀገራችንም ስርአት በህግ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን መሰረታዊ የህግ መርሆችንና የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመድፈን ስራውን እያከናወነ ቆይቷል፡፡ ከነዚህም አንዱ አስጠቂ ምስክርን በሚመለከት መሰረታዊ የህግ መርሆችን በመከተል ክፍተቱን ለመሙላት የተደረገው ጥረት ነው፡፡

ማስረጃ የማቅረብን የማሰማት ሀላፊነት ያለበት ወገን ማስረጃውን በማቅረብ ክርክሩን በሚያቀርበው ማስረጃ የማስረዳት ሀላፊነት አለበት፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ክርክሩን ያስረዳሉ የተባሉት ምስክሮች ከጉዳዩ ተቃራኒ በሆነ መልኩ በማስረዳት በጠራቸው ተከራካሪ ወገን ላይ ችግር ሊፈጥሩበት ይችላሉ፡፡ በተለይ በወንጀል ጉዳይ በምስክርነት የተጠሩ ሰዎች ቀደም ሲል ለፖሊስ ከሰጡት የምስክርነት ቃል በተለየ ሁኔታ በማስረዳት የተለየ ነገር ሲፈጥሩ ይታያሉ፡፡ ምስክሮቹ በዚህ አይነት ሁኔታ ቃላቸውን የሚለውጡት በተለያየ ምክንያት እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በምክንያትነት ሊጠቀሱ የሚችሉትን አንድ በአንድ ስንመለከት በመጀመርያ ለፖሊስ ቃላቸውን የሰጠት ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ይሆንና ፍርድ ቤት ቀርበው ለማስተካከል ይሆናል፡፡ ይኸ ከሆነ ደግሞ ሊያስመሰግናቸው የሚገባ እንጅ ሊያስወቅሳቸው የሚገባ

አይሆንም፡፡ በመሆኑም እነዚህን ምስክሮች አስጠቂ ምስክር አድረጎ ማየት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል ለፖሊስ ከሰጡት ቃል በተለየ መልኩ ለፍርድ ቤት ቃል የሚሰጡት በሚደርስባቸው ተጽእኖ ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህ አይነቱ ተጽእኖ በተለያየ ምክንያት ሊፈጠር ይችላል፡፡ በይበልጥ ጎልቶ የሚታወቀው የተከሰሱ ሰዎች ጥቃት ለማድረስ ባላቸው አቅም ምስክሮች የሚያውቁትን ነገር እንዲቀይሩ ሊያስገድዷቸው ይችላሉ፡፡ የምስክር ጥበቃ ህግንም መደንገግ ያስፈለገበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ማግኘት፣ማህበራዊ ጫና፣ወ.ዘ.ተ. በመሳሰሉ ምክንያቶች ትክክለኛ ቃላቸውን በመለወጥ ሊመሰክሩ ይችላሉ፡፡ የደረሰባቸው ተጥእኖ የተለያየ ቢሆንም ቀደም ሲል የሚያውቁትን ትክክለኛ ምስክርነት በመለወጥ ሌላ ቃል ከሰጡ ግን እነዚህ ምስክሮች በጠራቸው ወገን ላይ ሆን ብለው ጥቃት እንዲደርስ ያደረጉ በመሆናቸው አስጠቂ ምስክር ተብለው ይታወቃሉ፡፡

ዋና ጥያቄ የሚቀርበው በክርክሩ የተነሳው ነጥብ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ በመሆኑ፤በምስክር የሚገለጸው ቃል ዕምነት የሚጣልበት (reliable) ዋጋ ያለው (credible) መሆን አለበት፡፡ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚሰጥ የምስክርነት ቃል በተለያዩ ምክንያቶች ዕምነት የማይጣልበትና ዋጋ የሌለው ሊሆን ይችላል፡፡ ከነዚህም ምክንያቶቸ አንዱ በሚሰጠው የምስክርነት ቃል ላይ የሚታየው የተለያየ ነጥብ ነው፡፡ የምስክሩ ቃል በዋና ጥያቄና በመስቀልኛ ጥያቄ መለያየት፣የአንዱ ምስክር ቃል ከሌላው ምስክር ቃል የሚጋጭ ሆኖ መገኘት፣ምስክሩ ለፍርድ ቤት የሰጠው ቃልና ለፖሊስ የሰጠው ቃል የተለያየ ሆኖ መገኘት፣ወ.ዘ.ተ. የምስክሩን ቃል አስረጅነት ዕምነት የማይጣልበት እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ምስክሮች ተገቢ ባልሆነ ምክንያት ሳይሆን በማስታዎስ ችግር ለፖሊስ ከሰጡት ቃል በተለየ ለፍርድ ቤት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ ያለ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ አንዳንድ ሀገሮች መፍትሄ ያበጁለታል፡፡ ለምሳሌ እንደ ካናዳና አሜሪካ በመሳሰሉት አገሮች

ምስክሩ በትክክል የማታወስ ችግር ካጋጠመው፤ምስክሩ የዘነጋውን የሚያስታውስበት (re-freshing witness memory) ስርአት አላቸው፡፡ በዚህም አሰራር ምስክሩ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሚሰጠው ቃል በማስታወስ ችግር ለፖሊስ ከሰጠው የሚለይ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤቱን በማስፈቀድ ለፖሊስ የሰጠውን ቃል እንዲመለከተውና እንዲያስታውስ ማድረግ ይቻላል፡፡ በሃገራችን የህግ ስርአት ይህ አሰራር የሚደግፍ ህግ የለም፡፡ በሌላም በኩል ይህ እንዳይደረግ የሚከለክል ህግ የለም፡፡ ነገር ግን በልማድ በተለይም ሰነዶችን የሰሩ ሰወች ለምሳሌ እንደኦዲቶር በምስክርነት ተጠርተው በሚያስረዱበት ጊዜ አንዳንድ ነጥቦችን ከዘነጉ ሰነዶቹን በማሳየት እንዲያስታውሱ የሚደረግበት አሰራር አለ፡፡ በመሆኑም አሰራሩ በሰለጠነው አለም ተቀባይነት እስካለው ድረስ፣በእኛም የፍትህ አስተዳደር ለአንዳንድ ምስክሮች የሚፈቀድበት ሁኔታ ካለና አፈጻጸሙን በግልጽ የሚከለክል ህግ እስከሌለ ድረስ፤ ምስክሩ ነገሩን በማስታወስ ችግር ከዘነጋውና አስረጅነቱ ለትክክለኛ ፍትህ የሚረዳ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ፍርድ ቤቱን በማስፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡

## <u>መልመጃ</u>

(1) አስጠቂ ምስክርነትን በሚመለከት በሀገራችን በህግ በግልጽ የተደነገገው በአዋጅ ቁጥር 437/1997 ነው፡፡ ይህም አዋጅ የሚመለከተው የሙስና ወንጀሎችን ብቻ ነው፡፡ እርስዎ በሚያስችሉበት ወይም በሚከራከሩበት ሌላ ጉዳይ ምስክሩ አስጠቂ ሆኖ ከተገኘ የሚሰጠው ውሳኔ ምንድን ነው? ለሚሰጠውስ ውሳኔ መሰረት ተደርጎ የሚወሰደው መመዘኛ ምንድን ነው?

(2) ዋና ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ከሚነሱ መቃወሚያዎች አንዱ ጥያቄው መሪ ጥያቄ ነው የሚል ነው፡፡ እርስዎ በሚያስችሉበት ወይም በሚከራከሩበት ፍርድ ቤት በተግባር አንድን ጥያቄ መሪ ጥያቄ ነው ለማለት የሚሰጠው ምክንያት ምንድን ነው?

(3) በገለጻና በውይይት ከተገነዘቡት በመነሳት ከጽሁፉ ጋር የተያያዘው ምርመራ መሰረት አድርገው ዋና ጥያቄ ያቅርቡ፡፡

(4) በወንጀለኛ መቅጫ ስ-ስርአት ህግ ቁጥር 137 እንደተመለከተው በዋና ጥያቄ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ምስክሩ በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ስለሚያውቃቸው ነገሮች ብቻ ነው ይላል፡፡ በዚህ የህግ ድንጋጌ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚለው ሀረግ የሚመለከተው ምን ምን ጉዳዮችን ነው?

(5) ዋና ጥያቄ የማቅረብ መንገድ በሁለት አይነት መንገድ መከናዎን እንደሚችል ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ እነዚህም ክፍት የገለጻ ዘዴ (open narrative method) እና አንድ ባንድ የመጠየቅ ዘዴ (spesfic question metod) ተብለው ይታዎቃሉ፡፡ እርስዎ በሚቆሙበት ወይም በሚያስችሉበት ችሎት ያለው አሰራር ምን ይመስላል?

# ስድስት

## መስቀልኛ ጥያቄ

የተከሰሱ ሰዎች በህግ የተረጋገጡላቸው መብቶች በህግ-መንግስቱ አንቀጽ 20 ላይ በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩ መብቶች አንዱ የተከሰሱ ሰዎች በእነርሱ ላይ የቀረቡ ምስክሮችን መጠየቅ ይችላሉ የሚለው ነው፡፡ የተከሰሱ ሰዎች በእነርሱ ላይ የቀረቡ ሰዎችን መጠየቅ የሚችሉት ደግሞ የመስቀልኛ ጥያቄ በማቅረብ ነው፡፡ በመሆኑም መስቀልኛ ጥያቄ ማቅረብ የተከሰሱ ሰዎች ህገ-መንግስታዊ መብት መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡የወንጀል ስነ-ስርአት ድንጋጌዎችን ለሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህም ህገ-መንግስታዊ መሰረት ያላቸው ድንጋጌዎች( constitutional procedural rules ) እና መደበኛ የወንጀል ስነ-ስርአት ድንጋጌዎች( statutory criminal procedural rules ) በመባል ይታወቃሉ፡፡ በስነ-ስርአት ህጉ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች አንዱ የመስቀልኛ ጥያቄ ሲሆን፤ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ህገ-መንግስታዊ መሰረት ያለው በመሆኑ በመጀመርያው ምድብ ከሚካተቱ ድንጋጌዎች አንዱ ነው፡፡

የመስቀልኛ ጥያቄ የሚቀርበው በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ነው፡፡ አንድኛው ቀርቦ እየተሰማ ያለው ምስክር በዋና ጥያቄ የሰጠው መልስ እምነት የማይጣለልበት እና ዋጋ ሊሰጠው የማይገባ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የምስክሩ ቃል ትክክለኛ ቢሆንም፤ አንዳንድ ነጥቦችን ግልጽ እንዲሆኑ በማድረግ የራስን ክርክር ወይም መከላከያ ለማጠናከር ሊቀርብ ይችላል፡፡ በሀገራችን የወንጀል ስነ-ስርአት ህግ አንቀጽ 137 ንኡስ ቁጥር 3 እንደተመለከተው መስቀልኛ ጥያቄ የሚቀርበው ምስክሩ በዋና ጥያቄ የሰጠው መልስ የተሳሳተ አጠራጣሪ ወይም ሀሰት መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ከዚህ የህግ ድንጋጌ መረዳት እንደምንችለው የምስክሩ ቃል ሀሰት ወይም የተሳሳተ መሆኑን በማሳየት የምስክሩ ቃል እምነት የማይጣልበት

እና ዋጋ የሌለው መሆኑን ማሳመን ይቻላል። በሌላም በኩል አጠራጣሪ የሆነውን መልስ የራስን ክርክር በሚደግፍ መልኩ ግልጽ እንዲሆን በማድረግ በምስክሩ ቃል መደገፍ ይቻላል።

በመስቀልኛ ጥያቄ እራስን ለመከላከል የሚቻል መሆኑን ፀሀፊው የራሱን ተሞክሮ ማንሳት ይፈልጋል። ጊዜው በእኛ ዘመን አቆጣጠር በ1985 ዓ/ም ነው። በዚያን ጊዜ እኔ የደቡብ ወሎ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ በመሆን እሰራ ነበር። ዐቃቤ ህግ በተከሳሹ ላይ በመሰረተው ክስ ተከሳሹ በወነወጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 522 (1) (ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ ሟች እገሌ አባበሉን ሚስቴን አባልጓል በሚል ቂም በቀል በመያዝ፤በታጠቀው ዲሞፕቶር ጠመንጃ ተኩሶ በመግደሉ በፈጸመው ወንጀል መከሰሱን ገልጧል። ተከሳሹ በሰጠው ይምነት ክህደት ቃል ጥፋተኛ አይደለሁም በማለቱ ዐቃቤ ህግ አራት ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል። ቀርበው የተሰሙት ምስክሮች ተከሳሹ ሟቹን ሚስቴን አባልጓል በሚል ብክንያት በክሱ በተገለጸው ጊዜና ቦታ ሟቹን በያዘው ዲሞፕቶር ጠመንጃ ተኩሶ መግደሉን እንደሚያውቁ አስረድተዋል። የዐቃቤ ህግ ዋና ጥያቄ እንዳለቀ የተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ መስቀልኛ ጥያቄ አቅርቧል። የመጀመርያው ጥያቄ ሟች የሞተው በተከሳሹ ቤት አይደለም ወይ የሚል ሲሆን አራቱም ምሰክሮች ተመሳሳይ በሆነ ቃል ሟች የሞተው ተከሳሹ ቤት እንደሆነ ገልጸዋል። ሁለተኛው ጥያቄ በወቅቱ ሟች ከተከሳሽ ሚስትጋር ተንቶ አልነበረም ወይ የሚል ሲሆን፤ ምስክሮቹ በሰጡት መልስ በማረጋገጥ አስረድተዋል።

የዐቃቤ ህግ ማስረጃ በዚሁ የተጠቃለለ ሲሆን፤ፍርድቤቱ በሰጠው ብይን ተከሳሹ በተመሰከረበት መጠን ይከላከል ብሏል። ተከሳሹ  የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን በአቀረበው የጽሁፍ ማመልከቻ አረጋግጧል። ፍርድ ቤቱም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ዐቃቤ ህግ በተከሳሹ ጠቅሶ ያቀረበውን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 522ን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ 113 መሰረት በመለወጥ በተከሳሹ ላይ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 524 መሰረት የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቷል።

በዐቃቤ ህግ ክስ ተከሳሹ ሚቹን የገደለው ሚስቴን አባልጓል በሚል ቂም በቀል እንደነበር ተገልጥዋል፡፡ ነገር ግን ቀርቦ የተሰማው የአቃቤ ህግ ማስረጃ ተከሳሹ ሚቹን የገደለው ደምን በሚያፈላና ብርቱ ዝንባሌን በሚፈጥር ሁኔታ እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው በዋና ጥያቄ የተሰጠውን መልስ አጠራጣሪነት ግልጽ ለማድረግ የሚችል ጥያቄ በማንሳት፤የራስን ክርክር የሚደግፍ ወይም ለመከላከያ የሚሆን ሁኔታን በመስቀልኛ ጥያቄ መፍጠር የሚቻል መሆኑን ነው፡፡ ይህም ምሳሌ የመስቀልኛ ጥያቄ ሁል ግዜ የምስክሩ ቃል ሀሰት መሆኑን ብቻ ለማሳየት የሚቀርብ ብቻ ሳይሆን፤የምስክሩን ቃል መሰረት በማድረግም የሚፈለገውን መልስ ማግኘት እንደሚቻል የሚያሳይ ነው፡፡

መስቀልኛ ጥያቄን በሚመለከት የሚነሳው ሌላው ነጥብ የጥያቄውን ወሰን በሚመለከት ያለው ነው፡፡ በአንድ በኩል የመስቀልኛ ጥያቄ መመስረት ያለበት በዋናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ነው የሚል አስተያየት አለ፡፡ በሌላ በኩል ጥያቄው በዋናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ላይ ብቻ መወሰን የለበትም የሚል አስተያየጥ ይንጸባረቃል፡፡ በአገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 137 ንኡስ ቁጥር

3 እንደተገለጸው የመስቀልኛ ጥያቄ በዋናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ላይ ያለው ቃል ስህተት፣ የሚያጠራጥር ወይም ሃሰተኛ መሆኑን ለማሳየት የሚቀርብ ነው፡፡ በአሜሪካ ፌደራል ፍርድ ቤቶች መስቀልኛ ጥያቄ በዋና ጥያቄ ከተሰጠው መልስ ውጭ መቅረብ አይችልም፡፡ በዚችው አገር የክልል ፍርድ ቤቶች ግን ጥያቄው በዋና ጥያቄ ከተሰጠው መልስ ውጭም መቅረብ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ እንደ ኢንግላንድ አውስትራልያ እና ካናዳን በመሳሰሉ አገሮች መስቀልኛ ጥያቄ በዋና ጥያቄ ከተሰጠው መልስ በመዝለል ሊቀርብ ይችላል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ ነጥቦችን አንስቶ ማየት ተገቢ ሊሆን ይችላል። የመስቀልኛ ጥያቄ የሚቀርብበት አንድኛው ምክንያት የምስክሩ ቃል እምነት የማይጣልበት መሆኑን ለማሳየት ነው። የምስክሩ ቃል እምነት የማይጣልበት መሆኑን ለማሳየት ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ የምስክሩ ቃል እርስ በርሱ የሚጋጭ (inconsistent statement ) መሆኑን በተጨባጭ በመግለጽ ነው። ቃሉ እርስ በርሱ የሚጋጭ መሆኑን ለማስረዳት ከምናቀርባቸው ማስረጃዎች አንዱ ምስክሩ ለፍርድ ቤት ቀርቦ የሰጠው የምስክነት ቃል እና ቀደም ሲል ለፖሊስ የሰጠው ቃል የሚለያይ እንደሆነ በማስረዳት ነው። ምስክሩ በዋናው ጥያቄ ለፖሊስ የሰጠውን ቃል በተመለከተ የተነሳ ነገር ላይኖር ይችላል። ሆኖም መስቀልኛ ጥያቄ አቅራቢው ምስክሩ ለፍርድ ቤት የሰጠው ቃል ለፖሊስ ከሰጠውቃል ጋር የሚቃረን ሆኖ ካገኘው፤ይህንን በሚመለከት ለፖሊስ ቃል ስለመስጠቱ ቢጠይቅ ለፖሊስ ቃል ስለመስጠቱ በዋና ጥያቄ ያልተነሳ በመሆኑ ልትጠይቅ አትችልም ሊባል ነው ወይ? በዋናው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ላይ ያለው ቃል ስህተትና ሀሰተኛ መሆኑን ለማሳየት እስከሆነ ድረስ በመስቀልኛ ጥያቄው አግባብነት ላይ ጥያቄ ሊነሳ አይገባም። በመሆኑም የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 137 ድንጋጌ አተረጓጎም በዚህ መልኩ መታየት ይኖርበታል።

መስቀልኛ ጥያቄን ማቅረብ ልዩ እውቀትንና ክህሎትን ይጠይቃል። በዘልማድ እያደረግን ያለውን አሰራር ስንመለከት እራሳችንን ቆም ብለን መመልከት እንድንችል እንገደዳለን። መስቀልኛ ጥያቄ በሌላው ወገን ከተጠራው ምስክር ጋር የምናደርገው እሰጥ አገባ ሳይሆን፤ በጥበብና በዘዴ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን የምርመራ ዘዴ ነው። እስቴቨን ሉቤት የተባሉ ጸሀፊ Modern Trial Advocacy በተባለ መጽሀፋቸው በገጽ 79 ላይ፤The worst fears on examination-in-chief is usually that you have left something out. A poor cross examination on the other hand, can be truly disasterous. በመሆኑም ጥያቄውን በምናቀርብበት ጊዜ ተገቢውን ውጤት ለማምጣት ልንከተላቸው የሚገባን መሰረታዊ

መርሆች አሉ፡፡ እነዚህን መርሆዎች ተከትለን የምናከናውነው ስራ በመስቀልኛ ጥያቄ ልንደርስበት የምንፈልገውን ግብ እውን ለማድረግ ያስችለናል፡፡ እነዚህ መርሆዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

(1) **መሪ ጥያቄ ብቻ ማቅረብ** - በዋና ጥያቄ ጊዜ ካልተፈቀደ በስተቀር መሪ ጥያቄ ማቅረብ

እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ መስቀልኛ ጥያቄ ሲቀርብ ግን መሪ ጥያቄ ማቅረብ ይፈቀዳል፡፡ የነገሩ ሁኔታ የግድ የሚል ካልሆነ በስተቀር መሪ ያልሆነ ጥያቄ ማቅረብ አያስፈልግም፡፡ በዚህ ደረጃ ምስክሩ የሚፈልገውን ሳይሆን ጠያቂው የሚፈልገውን መልስ ስለሆነ የሚጠበቀው ጥያቄው የምርመራ ባህሪ ያለው ነው፡፡ መሪ ጥያቄ ምስክሩ እንዲመልስ የሚፈለገውን መልስ በውስጡ የያዘ ነው (leading question suggest the answer)፡፡ በክርክሩ በተገለጸው ጊዜ ምስክሩ ከተከሳሹ ጋር እንደነበር ለማሳወቅ ከተፈለገ፣ለምስክሩ የሚቀርበው ጥያቄ በዚህ ሰዓት አንተ ከተከሳሹ ጋር ነበርክ አይደል? ተብሎ ነው መጠየቅ ያለበት፡፡

(2) **ምስክሩን መቆጣጠር** - ውጤታማ መስቀልኛ ጥያቄ በተከታታይ እየቀረበ ስኬታማ መልስ ማስገኘት የሚያስችል ጥያቄ ለመፍጥር የሚያስችል ዕቅድ ውጤት ነው፡፡ ምስክሩ ከሚጠየቀው ጥያቄ ውጭ በመውጣት መልስ እነዲሰጥ የሚያስችል ሁኔታን መፍጠር ይህንን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ አያስችልም፡፡ መስቀልኛ ጥያቄ የሚያቀርበው ወገን ምስክሩ እያፈነገጠ ከሚጠየቀው ውጭ በመሄድ ተገቢ ያልሆነ መልስ እንዳይሰጥ ምስክሩን በተገቢው መንገድ ሊቆጣጠረው ይገባል፡፡ ምስክሩ ባለማወቅ ያፈነገጠ መልስ ሊሰጥ ይችላል፡፡ እንደዚህ ያለውን ምስክር ጥያቄውን በማስታወስ ከጥያው ጋር የተያያዘ መልስ እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ምስክር ከጥያቄው ያፈነገጠ መልስ የሚሰጠው ሆን ብሎ ተገቢውን መልስ

ላለመስጠት ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚህ ያለውን ምስክር በቀላሉ በማስታወስ ከጥያቄው ጋር የተያያዘ መልስ እንዲሰጥ ማድረግ ስለማይቻል ጠበቅ ባለ ቁጥጥር ከጥያቄው ጋር የተገናኘ መልስ እንዲሰጥ ማድረጋ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የምስክሩን ስም በመጥራት ከጥያቄው ያፈነገጠ መልስ መስጠት እንደማይችሉና ከጥያቄው ጋር የተያያዘ መልስ የመስጠት ሃላፊነት እንዳለባቸው ማስታወስና ተገቢውን መልስ መስጠት ካልቻሉ ከጥያቄው ጋር የተያያዘ መልስ እስከሚሰጡ ድረስ ጥያቄው እንደማይቋረጥ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

(3) **ጥያቄዎችን በሚገባ መቅረጽ** (frame the questions to best advantage)- ጥያቄዎችን በትክክል መቅረጽ መስቀልኛ ጥያቄ የሚያቀርበው ወገን የሚጠብቀውን መልስ ለማግኘት የሚያስችለውን ሁኔታ ይፈጥርለታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ የክርክር ሂደቶች እንደሚስተዋለው ጥያቄዎች የሚቀርቡት ጥንቃቄ በጎደለው መልኩ ስለሚሆን ውጤታማ ያለመሆን ሁኔታ ይታያል፡፡ ጥያቄዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ተፈላጊውን መልስ ለማግኘት በሚያስችል መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ በአንድ የመኪና ግጭት አደጋ ክርክር የሚገኝ የመስቀልኛ ጥያቄ አቅራቢ የመኪና ግጭቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ዝናብ ይዘንብ እንደነበር ምስክሩ እንዲመልስለት ከፈለገ ጥያቄውን መቅረጽ ያለበት አደጋው በሚፈጸምበት ጊዜ ዝናብ ይዘንብ ነበር አይደል? በማለት ነው፡፡

(4) **በግብ ላይ ማተኮር** (Be goal oriented)- የመስቀልኛ ጥያቄ የሚቀርበው ምስክሩ በዋናው ጥያቄ የሰጠው መልስ ትክክለኛ አለመሆኑን ወይም የምስክሩን ቃል የራስን ክርክር ለማጠናከር ለመጠቀም ነው፡፡ መስቀልኛ ጥያቄ አቅራቢው ከምስክሩ የሚፈልገውን መልስ ለማግኘት የተለያዩ ጥያቄዎችን ሊያነሳ ይችላል፡፡ በየተራ የሚቀርቡት ጥያቄዎች አንዳቸው ለአንዳቸው ግብአትነት ወይም አንዳቸው

የአንዳቸው ውጤት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ጥያቄዎች በሚቀርቡበት ጊዜ በመጨረሻ ልንደርስበት የምንፈልገውን ግብ ታሳቢ በማድረግ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ግብ የሚደረስበት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፤ ስራዎችን አቅጣጫ ለማስያዝ የሚያስችል ነው፡፡ ግቡ ምን እንደሆነ የማይታዎቅ እንቅስቃሴ ከመባዘን የዘለለ ውጤት አይኖረውም፡፡ ከዚህም አንጻር በመስቀልኛ ጥያቄ የሚቀርበውን ጉዳይ ለመለየት በመስቀልኛ ጥያቄው ሊደረስበት የሚገባውን ግብ መለየትና ማስቀመጥ ይገባል፡፡በዚህ መሰረት የሚደረግ የስራ እንቅስቃሴ ስራውን በአግባቡ ለመምራት ስለሚያስችል በግብ ላይ ያተኮረ የመስቀልኛ ጥያቄ ውጤታማነቱ የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡

(5) **የጥያቄውን ዓላማ ከምስክሩ መሰወር** (play your cards close to the vest) ማንኛውም በመስቀልኛ ጥያቄ የሚቀርብ ጉዳይ ምስክሩን ለመመርመር ባተኮረ ዓላማ ላይ መመስረት አለበት፡፡ጥያቄው በሚቀርብበት ጊዜ የመስቀልኛ አቅራቢው አላማ ምን እንደሆነ ምስክሩ በምን ዓይነት ሁኔታ ማወቅ የለበትም፡፡ ምስክሩ የምርመራው ዓላማ ምን እንደሆነ ከተረዳ (በተለይ ቅን ልቦና የጎደለው ምስክር ከሆነ) ጥያቄ አቅራቢው የሚፈልገውን መልስ እንዳያገኝ በሚያስችል መልኩ እንዲመልስ የሚረዳ ሁኔታ ይፈጠርለታል፡፡ መስቀልኛ ጥያቄ፤ ጥያቄ አቅራቢው ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ በማግኘትና ምስክሩ መፈናፈኛ እንዲያጣ በማድረግ ወደተገቢው ድምዳሜ ለመድረስ እንዲሰራ ግድ ይለዋል፡፡ በመሆኑም ይህንን ተግባር ስራ ላይ ለማዋል ከሚያስችሉ ዘዴዎች አንዱ ጥያቄው የሚቀርበትን ዓላማ ከምስክሩ መሰወር ነው፡፡

(6) **ከሁኔታዎች ጋር መጣጣም** (Be flexible and responsive) - በአብዛሀኛውን ጊዜ የመስቀልኛ ጥያቄ የሚያቀርብ ተከራካሪ ስለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች አስቀድሞ

መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡አንዳንድ ጊዜ ግን ያልታሰቡ አጋጣሚዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ የተዘጋጀንባቸው ነገሮች ብዙም ላይረዱን ይችላሉ፡፡ ምስክሩ በሚሰጠው መልስ ያልተጠበቀ ነገር ካጋጠመ ሂደቱን ወደተፈለገው መንገድ ለማምጣት ከእንግዳው መልስ ጋር በመጣጣም ሁኔታዎችን ለራስ ጥቅም ለማዋል በሚያስችል ሁኔታ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ አዳዲስ ሁኔታዎች እንዴት አድርገን እራሳችንን በማለማመድ ዓላማችንን ከዳር ለማድረስ እንደምንችል ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል፡፡

(7) **ግልጽ ቋንቋ መጠቀም** (Use plain language) መስቀልኛ ጥያቄ የምናቀርበው ምስክሩ የምንፈልገውን መልስ እንዲሰጠን ነው፡፡ ምስክሩ የምንፈልገውን መልስ ሊሰጠን የሚችለው ደግሞ የምናቀርብለት ጥያቄ ግልጽ ሲሆንለት ነው፡፡ የመስቀልኛ ጥያቄ በባህሪው ምስክሩ የሚፈልገውን መልስ ሳይሆን ጠያቂው የሚፈልገውን መልስ ለማግኘት የሚቀርብ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ጥያቄው ቀላልና ግልጽ በሆነ ቋንቋ መቅረብ ካልቻለ ምስክሩ ከጥያቄው ያፈነገጠ መልስ እንዲሰጥ ይዳርገዋል፡፡ በዚህ ርእስ በተራ ቁጥር 2 እንደተገለጠው ምስክሩ ያፈነገጠ መልስ እንዳይሰጥ መቆጣጠር እንደሚገባ የተገለጸ በመሆኑ፤እራሳችን በምንፈጥረው ችግር ምስክሩ ያፈነገጠ መልስ እንዲሰጥ ማድረግ አይኖርብንም፡፡

(8) **መልሱን እርግጠኛ መሆን** (securing the answer) በመስቀልኛ ጥያቄ ለሚቀርብ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ጥያቄውን የሚያቀርበው ሰው የሚፈልገው መሆን አለበት፡፡ በምንም ዓይነት በጠያቂው የማይፈለግ መልስ ሊሰጥ አይገባም፡፡ በጠያቂው ወገነወ በኩል እንዲህ ያለው ፍላጎት ቢኖርም፤እንዳንድ ጊዜ ምስክሩ ጥያቄ አቅራቢው የማይፈልገውን መልስ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህም የሚሆንበት በጥያቄ አቅራቢው በኩል በሚፈጸሙ ከጥያቄ አቀራረብ ጋር በሚያያዙ ምክንያቶች ነው፡፡ ምስክሩን

የሚመረምረው ወገን ለምስክሩ ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ ምስክሩ የሚፈልገውን መልስ እንደሚሰጠው እርግጠኛ መሆን አለበት፡፡ ምስክሩ የሚሰጠውን መልስ እርግጠኛ ካልሆነ ወይንም የማይፈለግ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳለ ካወቀ ጥያቄውን ከማቅረብ መቆጠብ አለበት፡፡ ለምሳሌ በሌሊት የተፈጸመን የወንጀል ድርጊት ለማስረዳት የቀረበ ምስክር ቃሉን ሲሰጥ በትክክል በአይኑ ያየ መሆኑን በማስረገጥ ከተናገረ፤ምንም እንኳ እንዴት ሊከታተል ቻለ የሚል ግምት ቢያሳድርም በሌላ በኩል ብርሀን ሊኖር እንደሚችል መገመት ይገባል፡፡ በመሆኑም ለምስክሩ በወቅቱ ብርሃን ነበር ወይ? የሚል ጥያቄን ለማቅረብ በወቅቱ በአካባቢው ብርሀን ስላለመኖሩ ተገቢ መረጃ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ ካልሆነ ምላሹ ባለተጠበቀ ሁኔታ አዎ ብርሀን ነበር የሚል ከሆነ የምስክሩን ቃል ዋጋ ለማሳጣት የቀረበው ጥያቄ የምስክሩን ቃል ተአማኒነት በማጠናከር ሊደመደም ይችላል፡፡

(9) **ከምስክሩ ጋር የሚስማማ ባህሪ መያዝ**(Estabilish an appropriate demeaminour toward the witness) በአንድ ክርክር የሚቀርቡ ምስክሮች ባህርይ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ምስክሮች ለመቀርብላቸው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ በመስጠት ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ በመፍጠር አጋዥ ሲሆኑ፤አንዳንድ ምስክሮች ግን በተቃራኒው ትክክለኛ መልስ ባለመስጠት ወይም ከሚጠየቀው ጥያቄ በማፈንገጥ ችግሮችን ሲፈጥሩ ይስተዋላሉ፡፡ በመርህ ደረጃ ምስክሮች የሚቀርቡት የፍትህ ስርአቱን ለማገዝ ነው ተብሎ ስለሚገመት ምስክሮችን በማፋጠጥ ልንጠይቃቸው አይገባም፡፡ ሆኖም ይኸ ሁልጊዜ እውነት ሊሆን ስለማይችል የምስክሮቹ ባህሪ የማፋጠጥ ስልትን እንድንከተል

የሚያስገድድ ከሆነ በዚሁ መልኩ ስራችንን ማከናወን ይኖርብናል፡፡ ለሚጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ካልፈለጉ ወይንም ከጥያቄው በማፈንገጥ መልስ

የሚሰጡ ከሆነ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ምስክሮችን ማፋጠጥና መመርመር ይገባል፡፡ በመሆኑም በአንድ ክርክር የመስቀልኛ ጥያቄ የሚያቀርብ ወገን ለምስክሩ ያለውን አቀራረብ መወሰን ያለበት ምስክሩ በሚያሳየው ባህሪ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡

ለምስክሩ ዋና ጥያቄ ከቀረበ በኋላ የሚቀርበው መስቀልኛ ጥያቄ ከሁለት ምክንያቶች አንዱን ይዞ መቅረብ አለበት፡፡ አንድኛው ምስክሩ በዋና ጥያቄ የሰጠው መልስ የተሳሳተ ወይም ሃሰት መሆኑን ለማሳየት ሲሆን፤ሌላው በምስክሩ ቃል የተነገረውን ግልጽ ያልሆነ ቃል ግልጽ እንዲሆን በማድረግ የራስን ክርክር ለማጠናከር ነው፡፡ በምስክሩ ቃል ግልጽ ሆኖ ያልተገለጸውን ነገር ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ የሚደረገው እንቅስቃሴ ብዙም አስቸጋሪ ላይሆን ይችላል፡፡ አስቸጋሪ የሚሆነው በምስክሩ የተነገረው ነገር ትክክለኛ አይደለም ወይም ሀሰት ነው በማለት ምስክሩን ለመመርመር የሚደረገው ጥረት ነው፡፡ ከላይ ከተራ ቁጥር 1-9 የተዘረዘሩት መስቀልኛ ጥያቄ የማቅረብ መርሆዎች ምስክሩን ለመመርመር በምናደርገው እንቅስቃሴ አይነተኛ መሳርያዎች በመሆናቸው በተገቢው ሁኔታ ልንገለገልባቸው ይገባል፡፡ በአብዛሀኛው በተግባር እንደሚስተዋለው እነዚህን የመስቀልኛ ጥያቄ አጠያየቅ ዘዴወች ለመጠቀም የሚደረገው እንቅስቃሴ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ሌላው ይቅር መሪ ጥያቄን በሚመለከት በተገቢው ሁኔታ ስራ ላይ ውሏል ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡

<u>**መልመጃ**</u>

(1) በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 137 መሰረት የመምራት ጥያቄዎችን በመስቀልኛ መጠየቅ ይቻላል፡፡ በመስቀልኛ ጥያቄ የመምራት ጥያቄ ማቅረብ የተፈቀደበት ዋንኛ ምክንያት ምንድን ነው?

(2) በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 137 እንደተመለከተው በመስቀልኛ ጥያቄ የሚቀርበው ጥያቄ በዋና ጥያቄ በተሰጠው መልስ ውስጥ ያለውን የስህተት፤የሚያጠራጥር

ወይም እውነት ያልሆነውን ቃል ለማስተባበል የሚቀርብ ነው፡፡ አንዳንድ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች በሚሰጡት አስተያየት በዚህ ድንጋጌ መንፈስ ጥያቄው በዋና ጥያቄ ከተነሳው ነጥብ ውጭ መሆን የለበትም ይላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የመስቀልኛ ጥያቄ አላማ ምስክሩ በዋና ጥያቄ የሰጠው መልስ ትክክል አለመሆኑን፤አጠራጣሪ መሆኑን ወይም እምነት የማይጣልበት መሆኑን ለማሳየት እስከሆነ ድረስ በዋና ጥያቄ በቀረበው ጥያቄ ባለመወሰን ጥያቄውን ማቅረብ ይቻላል ይላሉ፡፡ እርስዎ የትኛውን አስተያት ይቀበላሉ? ለአሰተያየትዎስ የሚሰጡት ምክንያት ምንድን ነው?

(3) በወንጀል ጉዳይ ለማስረዳት የሚቀርቡ አንዳንድ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ቀደም ሲል ለፖሊስ ከሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር የሚለያይ ቃል ሊሰጡ ወይንም ለፖሊስ የሰጡትን ቃል ለፍርድ ቤት ላይሰጡት ይችላሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ እርስዎ የተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ ቢሆኑ በምን መልኩ ይጠቀሙበታል? የሚጠቀሙበት ከሆነስ ለአቤቱታዎ መሰረት የሚያደርጉት የህግ ድንጋጌ የትኛው ነው?

(4) ቀደም ሲል ከጽሁፉ ጋር የተያያዘውን ሞዴል የፖሊስ ምርመራ መሰረት በማድረግ ዋና ጥያቄ አዘጋጅተው ማቅረብዎ ይታዎቃል፡፡ አሁን ደግሞ ስለመስቀልኛ ጥያቄ ከተደረገው ገለጻና ውይይት ተገቢ ግንዛቤ እንደያዙ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ሞዴል የፖሊስ ምርመራውን፤የተደረገውን ገለጻና ውይይት እና በዋና ጥያቄ የቀረበውን መሰረት በማድረግ መስቀልኛ ጥያቄ አዘጋጅተው ያቅርቡ?

(5) በመስቀልኛ ጥያቄ ጊዜ መሪ ያልሆነ ጥያቄ (open ended) ለማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ ምንድን ነው? ይህንን አይነቱንስ ጥያቄ በመርህ ደረጃ መቅረብ እንደሌለበት የሚመከረው ለምንድን ነው?

# ሰባት

## የመዝጊያ ንግግር (closing argument)

በፍትሀ-ብሄርም ሆነ በወንጀል የፍትህ አስተዳደር ስርአት የግራ ቀኙ ማስረጃ ከተጠናቀቀ በኂላ የመዝጊያ ንግግር ይቀርባል፡፡ ቀደም ሲል የመክፈቻ ንግግር ለማስተዋዎቅ እንጅ ለማሳመን ተብሎ እንደማይቀርብ እና በገለልተኛነት መቅረብ እንዳለበት ተገልጧል፡፡ የመዝጊያ ንግግር ግን ለማሳመን ተብሎ የሚቀርብ በመሆኑ ገለልተኛ በመሆን ሳይሆን የራስን በማግዘፍ የሌላውን ወገን ክርክር ዋጋ በማሳጣት የሚቀርብ ነው፡፡ ይህ ሲሆን ግን የሌላውን ክርክር ዋጋ ለማሳጣት የሚቀርበው የማሳመን ክርክር ህግን መሰረት ያደረገ እንጅ በሌላ ሁኔታ እንዲቀርብ አያስፈልግም፡፡ማንኛውም ሰው የሚያቀርበው የመዝጊያ ንግግር ከሌላው ጋር ተመሳሳይ እንዲህን አይጠበቅም፡፡እንደ ጉዳዩን እንደ ክርክሩ ይዘት አቀራረቡ ሊለያይ ይችላል፡፡ እንደዚህ ሲባል ግን ለሁሉም ክርክሮች የጋራ ተደርገው የሚወሰዱ ነጥቦች የሉም ማለት አይደለም፡፡

ይህንንም በሚመለከት ጀምስ ደብሊው ጅንስ የተባሉ ጸሀፊ Trial Advocacy በተባለ መጽሀፋቸው በገጽ 480 ላይ፤ The closing argument is an exercise in persuasion.To that extent it should meet the test of any good persuasive effprt.Those universal rules developed over the age of debetersand rhetorician merits the study of anyone seeking to become an effective advocate but we will not incorporate such universalities here. We shall limit ourselves to those unique circumstances which characterize the legal process and render the closing argument a singular form of persuasion.

በሀገራችን የህግ ስርአት የመዝጊያ ንግግርን በሚመለከት በፍትሀ-ብሄር ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 259 እና በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 148 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በሁለቱም የህግ ድንጋጌዎች መሰረት የመዝጊያ ንግግር የሚቀርበው የክሳሽና የተከሳሽ ማስረጃ ተሰምቶ ካለቀ በኂላ ነው፡፡ የመዝጊያ ንግግር በመጀመርያ ማቅረብ ያለበት ማን ነው? የሚለውን በሚመለከት የተለያዩ ሀገሮች የተለያየ አካሄድ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ በተወሰኑ ስቴትስ የመዝጊያ ንግግር የሚጀምረው ከሳሽ ሲሆን፤በአንዳንዶቹ ደግሞ የሚጀምረው ተከሳሽ ነው፡፡ እንደ ፈረንሳይና ጀርመን በመሳሰሉት አገሮች ደግሞ ተከሳሹ ንግግሩን የሚያደርገው ከሳሹ ካቀረበ በኂላ ነው፡፡ የመዝጊያ ንግግር እስከ ማስረጃ ማጠናቀቅ ድረስ ያለውን ሂደት መሰረት በማድረግ የሚቀርብና የአንድኛው ሀሳብ በሌላው ላይ ተመርኩዞ የሚሰጥ ባለመሆኑ ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ ቢጀምረው የሚኖረው ለውጥ የለም፡፡ ወደሀገራችን ህጎች ስንመጣ  በፍትሀ ብሄር ስነ-ስርአት ህግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ያሉት ቅደም ተከተሎች ይለያያሉ፡፡ በፍትሀ ብሄር የሚቀርበውን የመዝጊያ ንግግር የሚጀምረው ተከሳሽ ሲሆን በወንጀል የሚቀርበውን የመዝጊያ ንግግር የሚጀምረው ከሳሽ ነው፡፡

የመዝጊያ ንግግር የሚደረገው ማስረጃ ተሰምቶ ካለቀ በኂላ ነው፡፡ የአንድኛው ወገን የመዝጊያ ንግግር በሌላው ወገን የመዝጊያ ንግግር ላይ ተመስርቶ ስለማይፈጸም፤በክርክሩ ሂደት ከተገለጹት የፍሬ ነገሮች በስተቀር አዲስ ሀሳብን ማቅረብ አይቻልም፡፡ በመዝጊያ ንግግር የሚቀርበው ሀሳብ በክርክሩ ሂደት የተነሱት ነጥቦች የሚያሻሙና ግልጽነት የሚጎላቸው ሆነው በተገኙ ጊዜ

አጥጋቢና ምክንያታዊ በሆነ ክርክር ውሳኔ የሚሰጠውን አካል ለማሳመን የሚደረግ በመሆኑ፤ግልጽ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጊዜን ማጥፋት አያስፈልግም፡፡ ካያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል እንዲሉ፤ውሳኔ የሚሰጡት ሰዎች አጥጋቢና ምክንያታዊ በሆነ ክርክር የሚያምኑ

በመሆናቸው በጥሩ ሁኔታ የሚቀርብ የመዝጊያ ንግግር በፍርድ ሂደቱ ውጤታማ ለመሆን ያስችላል፡፡

በተግባር እንደሚስተዋለው የመዝጊያ ንግግር የመፋረጃ ሀሳብ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ቃሉ በህጉ ከተቀመጠው መለየቱ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ አፈጻጻሙም አላማውን የተከተለ አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ ማስረጃ ተሰምቶ ካበቃ በኋላ ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ ላይ ከሚሰጣቸው ትዛዞች አንዱ ግራ ቀኙ የመፋረጃ ሀሳብ ካላቸው በመዝገብ ቤት በኩል ገቢ ያድርጉት የሚል ነው፡፡ የመዝጊያ ንግግር በቃል ወይንም በጽሁፍ መቅረብ የሚችል ሲሆን፤በየትኛውም አይነት ዘዴ ቢቀርብም በችሎት መሰማት አለበት፡፡ የመዝጊያ ንግግር ማቅረብ መብት በመሆኑ፤የመብቱ ባለቤት በራሱ ፈቃድ ካልተወው በስተቀር በተግባር በሚታየው አሰራር በመብቱ ላይ ጫና ሊደረግበት አይገባም፡፡

አንድኛው ወገን በሚያቀርበው የመዝጊያ ንግግር ላይ ሌላው ወገን መቃወሚያም ሆነ አስተያየት ማቅረብ አይፈቀድለትም፡፡ በፍርዱ ሂደት ይህ ተግባር የሚፈጸመው ተከራካሪ ወገኖች ክርክርና ማስረጃ አቅርበው ካጠናቀቁ በኋላ በመሆኑና የመዝጊያ ንግግሩም የሚመሰረተው በቀረቡት

ጉዳዮች ላይ ብቻ በመወሰን በመሆኑ፤ከስነ-ስርአት ህግ አላማ አንጻር ግራ ቀኙን ማመላለስ አግባብነት አይኖረውም:: በዚህ ደረጃ እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በሚያቀርበው የመዝጊያ ንግግር በድጋሚ ሊያስተካክል የሚችልበት እድል ስለማይኖረው ተገቢውን ትጋትና ጥንቃቄ ሊያደረወግ ይገባዋል፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች ውሳኔ የሚሰጠውን አካል ለማሳመን የሚቀርብ የመዝጊያ ንግግር እንዴት መዘጋጀት እንዳለበት ይረዳሉ፡፡

**(ሀ) ጥሩ የሀሳብ ማቅረቢያ (outline) ማዘጋጀት-** በትክክል የተዘጋጀ የሃሳብ ማቅረቢያ ቅደም ተከተል ክርክርን በትክክል ለማቅረብ ከማስቻሉም በላይ የፍሬ ጉዳዮች መዘንጋት አደጋን ያስወግዳል፡፡ ሀሳብን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ጉዳዩን የሚከታተለው ክፍል በቀላሉ ጉዳዩን

ለመረዳት ስለሚያስችለው ነገሩን ለመከታተል ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ ያደርገዋል፡፡ ንግግሩንም የሚያቀርበው ወገንም ቢሆን ሀሳቡን በትክክል ማስቀመጥ እንዲችል ስለሚረዳው ውሳኔ የሚሰጠውን አካል ለማሳመን አመች ሁኔታን ይፈጥርለታል፡፡

**(ለ) ማስረጃዎችን መከለስ** ( review your evidence)- የመዝጊያ ንግግር የትኩረት አቅጣጫ ለክርክሩ የቀረቡ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ በማስረጃዎች ላይ የሚስተዋሉ ግልጽነት የጎደላቸው እና አሻሚ የሆኑ ነጥቦችን በመለየት የራስን አቋም የሚያጠናክርና የሌላውን ወገን ክርክር የሚያዳክም በምክንያት ላይ የተመሰረተ ክርክር ለማቅረብ እንዲቻል ማስረጃዎችን በሚገባ መመርመር ይገባል፡፡ ማስረጃዎችን

የመመርመሩና የመከለሱ ሂደት በጣም አድካሚ ሊሆን ይችላል፡፡ የመዝጊያ ንግግር ማጠንጠኛው ነጥብ ይኸው ስለሚሆን ሁኔታዎች የሚጠይቁትን ሁሉ ለማድረግ መዘጋጀት ይገባል፡፡

**(ሐ) የሌላውን ወገን ክርክር ማጥቃት** (attack the opposition case)- የመዝጊያ ንግግር የሚቀርበው የራስን ጉዳይ ትክክለኝነት ለማሳየት ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ወገን ክርክርና ማስረጃ ትክክል አለመሆን ለማሳየት ነው፡፡ የሌላው ወገን ክርክርና ማስረጃ ትክክል አለመሆኑን ለማሳየት ክርክሩንና ማስረጃውን በሚገባ ማጥናትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህም እረገድ በማስረጃዎቹ ውስጥ የሚታዩ ክፍተቶችንና መጣረሶችን (inconsistency) በአግባቡ መለየት፤የሌላውን ወገን ክርክር ዋጋ ለማሳጣት ከሚጠቅሙ ዘዴዎች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

**(መ) ተገቢ ልምምድ ማድረግ** (practice the closing argument)- የልምምዱ ከባድነት ውጊያውን ቀላል ያደርገዋል የሚባል አባባል አለ፡፡ በሌላም አነጋገር ልምምድ ሙሉ ያደርጋል(practice makes perfect) ይባላል፡፡ በተግባር በችሎት ከሚስተዋሉ ችግሮች አንዱ ከጉዳዩ ጋር በተገቢው ሁኔታ አለመናበብና ተገቢ ዝግጅት አለማድረግ ነው፡፡ ተገቢ ዝግጅት

ማድረግ ማለት ደግሞ ጉዳዩን መለማመድ ማለት ነው፡፡ ችሎቶች ሰዎች አቤቱታቸውን የሚያቀርቡባቸው ቦታዎች ቢሆኑም፤ከሌላ ቦታ በተለየ የሚፈጥሩት ድባብ አለ፡፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ሰዎች ማቅረብ የሚገባቸውን ሀሳብ

ሊዘነጉ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ የመሳሰሉትን ችግሮች ለመፍታት አስቀድሞ መዘጋጀትና ልምምድ ማድረግ ምትክ የማይገኝለት መፍትሄ ነው፡፡

**(ሠ) የሌላውን ሀሳብ መገመት** (anticipate the openion of the other side) ከሳሽ ተከሳሽ የሚለውን ባወቀ ኖሮ ክስ ባልመሰረተ ነበር የሚል አባባል አለ፡፡ በሌላው ወገን በኩል ያለውን ሁኔታ በሚገባ ማወቅ ስለምንወስደው እርምጃ ተገቢ ጥንቃቄ እንድናደርግ ይረዳናል፡፡ በመዝጊያ ንግግር የምናቀርበው ማጠቃልያ ሀሳብ በሌላው ወገን የሚቀርበውን ሀሳብ ለማወቅ እድል ሳይኖረን የምናቀርበው በመሆኑ ሌላው ወገን ሊያነሳቸው የሚችሉ ነጥቦችን በትክክል መገመት ይኖርብናል፡፡ ከዚህም አንጻር እራስን በሌላው ተከራካሪ በኩል አስቀምጦ ጉዳዩን መመልከት ይገባል፡፡

## <u>መልመጃ</u>

(1) በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርአት ህግ ቁጥር 148 የመዝጊያ ንግግር የክርክሩ ማቆሚያ ንግግር ተብሎ ነው የተገለጠው፡፡ በልማድ ግን የመፋረጃ ሀሳብ ተብሎ ነው የሚታወቀው፡፡ የመፋረጃ ሀሳብ የሚለው ቃል መነሻው ምንድን ነው? የመፋረጃ ሀሳብ የክርክር ማቆሚያ ንግግርን ይወክላል የምንል ከሆነስ፤በተግባር የመፋረጃ ሀሳብ ተብሎ የሚቀርበው ህጉንና የህጉን መንፈስ የተከተለ ነው ወይ?

(2) በዚህ ጽሁፍ መጨረሻ የተያያዘ ሞዴል የፖሊስ የምርመራ መዝገብ አለ፡፡ ይህንንና በስልጠናው በሌሎች ርእሰ ጉዳዮች የተከናዎኑትን ጉዳዮች በመያዝ የክርክር ማቆሚያ ንግግር ያዘጋጁ?

## ስምንት

## የመቃወሚያ ነጥቦች

በቃል ክርክር ሂደት ከሚከናወኑ ተግባራት አንዱ ማስረጃን በሚመለከት የሚነሳ መቃወሚያ ነው፡፡ አንድ ተከራካሪ ወገን ሌላው ተከራካሪ ወገን የቀረበውን ወይንም የተነሳውን ነጥብ በተለያዩ ምክንያት ተገቢ አይደለም ወይንም ሊቀርብና ሊታይ አይገባውም በማለት የሚያቀርበው ትችት መቃወሚያ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ተገቢ አይደለም ወይንም ሊቀርብ አይገባም የሚባለው ነጥብ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው የህግ ወይንም መሰረታዊ በሆነ የህግ መርህ መሰረት ሲኖረው ነው፡፡ ከተከራካሪው ወገን ፍላጎት አንጻር ሲታይ አንድ ነጥብ ተገቢ መስሎ ሊታይ ቢችልም፤ በመቃወሚያ ነጥብነት ሊመዘን የሚችለው ሊጠቀስ በሚችል መመዘኛ እይታ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

ይህን በሚመለከት ጀምስ ደብሊው ጅንስ፤ትርያል አድቮኬሲ፤በተባለ መጽሀፋቸው፣An objection is adevice by which we call to the attention of the trial judge any imminent, existing or excuted impropriety.በማለት ይገልጹታል፡፡ መቃወሚያ የሚለው ቃል በማናቸውም የክርክር ደረጃ የሚቀርብ በመሆኑ፤ከዚህ ጽሁፍ ጋር በተያያዘግን ልንመለከተው የሚገባን የማስረጃን አቀራረብ በተመለከተ ሊሆን ይገባል፡፡

በሀገራችን የክርክር ስርአት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መቃወሚያ ይቀርባል፡፡ አንዳንድ ነጥቦች ከተከራካሪው ፍላጎት የዘለለ ድጋፍ የሚያስገኙላቸው ምክንያት ሳይኖራቸው እየቀረ ውድቅ ሲደረጉ ይታያሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ አንደኛው በአጠቃላይ መቃወሚያ በመሆን መቅረብ የማይገባው በመሆኑ ሲሆን፤ሁለተኛው ደግሞ ነገሩ በመቃወሚያነት መቅረብ የሚችል ሆኖ ነገር ግን አሳማኝ በሚሆን መልኩ ባለመቅረቡ ውድቅ የሚደረግ በመሆኑ ነው፡፡ የመጀመርያው ስለመቃወሚያ አቀራረብ በቂ ግንዛቤ ካለመኖር

የሚፈጠር ሲሆን፤ሁለተኛው ደግሞ ከግንዛቤ ችግር የሚመነጭ ሳይሆን ማስረዳት ባለመቻል የሚፈጠር ነው፡፡ በአንድ ጉዳይ ተከራካሪ የሆነ ወገን በህግ ተቀባይነት ያለውን ነጥብ ተቀባይነት የለውም ሊቀርብ አይገባም ብሎ ቢከራከር በቂ የህግ ግንዛቤ ካለመያዝ የሚመነጭ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በህግ ተቀባይነት የለውም የተባለውን ጉዳይ በመቃወሚያነት ያቀረበ ተከራካሪ የሁኔታውን መኖር ወይም አለመኖር አላረጋገጥክም ተብሎ መቃወሚያው ውድቅ ቢደረግበት ከግንዛቤ ጉድለት የመጣ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ለምሳሌ በወንጀል ጉዳይ በአንድ ተከሳሽ ላይ ከሚቀርብበት ማስረጃዎች አንዱ ለፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 35 መሰረት የሰጠው ቃል ነው፡፡ ተከሳሹ ይህ አይነቱ ማስረጃ ሊቀርብብኝ አይገባም በማለት ተቃውሞ ቢያቀርብ መቃወሚያው የህግ መሰረት ስሌለለው የህጉ ግንዛቤ እጥረት እንዳለበት ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ቃሌን ለፍርድ ቤት በምሰጥበት ጊዜ በፖሊስ ጣቢያ ስለነበርኩ የሚደርስብኝን ተጽእኖ በመፍራት የሰጠሁት በመሆኑ በማስረጃነት ሊቀርብ አይገባም በማለት ቢከራከርና ማስረዳት አልቻልክም ተባሎ መቃወሚያው ውድቅ ቢሆን ከህግ ግንዛቤ ችግር የመጣ አይሆንም፡፡

ከላይ ለመግለጥ እንደተሞከረው መቃወሚያ የህግ ወይንም መሰረታዊ የህግ መርህ መሰረት ሊኖረው ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ወይም ላለመስጠት ምክንያታዊ ሊሆን ይገባል፡፡ በወንጀልም ሆነ በፍትሀ ብሄር የፍትህ አስተዳደር በሚቀርቡ ክርክሮች መሰረታዊ ተደርገው የሚወሰዱ የመቃወሚያ ነጥቦች እንደሚከተለው በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡

(ሀ) መሪ ጥያቄ- መሪ ጥያቄ ካልተፈቀደ በስተቀር በዋና ጥያቄ ጊዜ መቅረረብ አይችልም፡፡ በመስቀልኛ ጥያቄ ጊዜ ደግሞ ጥያቄ መቅረብ ያለበት በመሪ ጥያቄ መልክ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም በዋና ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄ ከተጠየቀ ማስረጃው የቀረበበት ወገን ጥያቄውና መልሱ ውድቅ እንዲደረግለት መቃወሚያ ማቅረብ ይችላል፡፡ ብዙውን ጊዜ በፍርድ ቤቶቻችን በሚደረጉ ክርክሮች ይህ ነጥብ በመቃወሚያነት የሚቅርብ ሲሆን፤አንዳንድ

ጊዜ ጥያቄው መሪ ጥያቄ ሳይሆን መቃወሚያ የሚቀርብበትም ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት መሪ ጥያቄ ምን ማለት ነው በሚለው ነጥብ ዙሪያ የሚታይ የግንዛቤ ችግር ነው፡፡ በተከታታይ በተከናወኑ ስልጠናወች መገንዘብ እንደቻልኩት ( ፕሪዝን ፎሎው ሽፕ ኢተዮጵያ ከፍትህ ትምህርት ማህበረሰብ ካናዳ ጋር በመተባበር ባዘጋጀው ስልጠናና፤የፌደራል ፍትህ አካላት ባለሞያወች ስልጠና ማእከል በተሰጡ ስልጠናዎች እንደተገነዘብኩት ) ቁጥራቸው አነስተኛ ነው የማይባል ዳኞችና አቃቤያነህግ መሪ ጥያቄ ማለት መልሱ አወን ወይም አይደለም የሚል ነው የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ የቀረበው ጥያቄ ለመልስ ሰጭው አወን ወይንም አይደለም የሚል የመልስ አማራጭ የሚሰጠው ከሆነ ጥያቄው መሪ ጥያቄ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም፡፡ አንድ ጥያቄ መሪ ጥያቄ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው ጥያቄው መልሱን በቀጥታ ለተጠያቂው የሚገልጽ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

**(ለ) አግባብነት-** በክርክር ሂደት ለማስረዳት የሚቀርብ ፍሬ ነገር በክርክሩ ከተያዘው ጉዳይ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህንን በሚመለከት ብላክስ ሎው መዝገበ ቃላት ‹‹ ማስረጃ ፍሬ ነገርን ወይንም በጭብጥነት የተያዘን ጉዳይ መኖር ወይም አለመኖርን አስመልክቶ ውሳኔ ሰጭውን ክፍል የማሳመን ውጤት ለመፍጠር ታቅዶ የሚቀርብ ማንኛውም ፍሬ ነገር ነው፡፡ ›› በማለት ይገልጸዋል፡፡ በሀገራችንም ታዋቂው ምሁር አቶ አለማዬሁ ሀይሌ የኤክስፐርት ማስረጃ በተባለው ጽሁፋቸው በገጽ 56 ላይ ‹‹ ማስረጃ ለፍርድ ቤት ግምት መሰረት በመሆን ውሳኔ ሊያሰጡ ከሚችሉ ከነዚህ ፍሬ ነገሮች በመነሳት ግምት የሚወሰድበት ነጥብ ላይ የሚረስበት ስርአት ነው፡፡ ››በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከነዚህ ሁለት የሀሳብ ምንጮች በመነሳት የያዝነው ጉዳይ ስንመለከት በማስረጃው የሚቀርበው አስረጅነት በክርክሩ በተያዘው ጭብጥ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት የሚቀርብ በመሆኑ ከጉዳዩ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ግንኙነት ከሌለው ግን በማስረጃው የተነገረው ወይንም የተገለጸው ፍሬ ነገር አግባብነት የለውም ይባላል፡፡ በመሆኑም

በማስረጃው የሚቀርበው ፍሬ ነገር አግባብነት ከሌለው ማስረጃው የሚወርብበት ወገን መቃወሚያ አድርጎ ሊያቀርበው ይችላል፡፡

(ሐ) ተቀባይነት- የማስረጃ ተቀባይነት የሚወሰነው በህግ ነው፡፡ የሚቀርበው ማስረጃ አከራካሪ የሆነውን ጉዳይ ለማስረዳት መቅረብ ይችላል ወይንስ አይችልም የሚለውን ነጥብ ለመወሰን ህግን መመልከት ይገባል፡፡ የማስረጃው አሳማኝነት አስተማማኝ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ብቻ ግን ማስረጃውን ለመጠቀም ስለማይቻል የግድ ማስረጃው የተያዘውን ፍሬ ነገር ለማስረዳት መቅረብ እንደሚችል የሚመለከተውን የህግ ድንጋጌ መመርመር ይገባል፡፡ ለምሳሌ በፍትሀ ብሄር ህግ ቁጥር 2472 እንደተመለከተው ከብር 500 በላይ የሆነን የብድር ውልን ማስረዳት የሚቻለው በጽሁፍ የተደረገውን የብድር ውል በማቅረብ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ሲሆን፤ከዚህ ውጭ ሌላ ማናቸውንም አይነት ማሰረጃ ማቅረብ አይቻልም፡፡ አንድ ሰው ብር 2000 ለአንድ ሰው 50 ሰወች ባሉበት ቦታ እነሱን እማኝ አድርጎ ቢያበድርና የተበደረው ሰው የተበደርኩት ገንዘብ የለም በማለት ቢከራከረው፤ምንም እንኳ አስረጂነታቸው ምንም የሚያጠራጥር ባይሆንም ተቀባይነት ግን ሊኖረው አይችልም፡፡ በሌላ በኩል ለፖሊስ በወንጀለኛ መቅጫ ህገ ስነ ሰስርአት 27 መሰረት የተሰጠ የተከሳሽነት ቃል ክሱን ለማስረዳት ብቻውን ክብደት የሌለው ቢሆንም፤ቀርቦ ለመታየት ተቀባይነት አለው፡፡

ስለማስረጃ ተቀባይነት ሲነሳ በሀገራችን የህግ ስርአት መታየት የሚኖርበት አንድ ነጥብ አለ፡፡ በሀገራችን ህግ መንግስት አንቀጽ 19 (5) እንደተገለጸው ‹‹ የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይንም ማንኛውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ጠቀባይነት የለውም፡፡ ››ይላል፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ የሚለውን በሚመለከት የተለያዩ አስተያየቶች ይሰጣሉ፡፡ አንድኛው አስተያየት በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ የሚለው የሚመለከተው የተከሳሽነት ቃል ብቻ የሚመለከት ነው የሚል ሲሆን፤ ሌላው በኩል ደግሞ ከተከሳሽነት ቃል በተጨማሪ

ማንኛውንም በማስገደድ የተገኘን ማስረጃ የሚያካትት ነው በማለት አስተያየታቸውን ያቀርባሉ፡፡

ከእነዚህ አስተያየቶች የትኛው ትክክል ነው የሚለው የጽሁፉ አላማ ባይሆንም ምክንያታዊ በሆነ መንገድ በመመልከት ተገቢ ነገር ማስቀመጥ ይገባል፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት ከሚለው አርፍተ ነገር አስቀድሞ ሌላ አርፍተ ነገር ያለ ሲሆን፤ ሀሁለቱም አርፍተ ነገሮች የተቀመጡት በአንድ ፓራግራፍ ስር ነው፡፡ ከሁለቱ አርፍተ ነገሮች ውጭ ሌላ አርፍተ ነገር በፓራግራፉ ውስጥ የለም፡፡ ከጽሁፉ አደረጃጀት አንጻር ተከታዩ አርፍተ ነገር ከቀደመው አርፍተ ነገር ጋር ተያዞ መነበብ ስላለበት ብቻውን ተነጥሎ መታየት የለበትም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በወንጀል የፍትህ አስተዳደር ማስረጃን ለማግኘት የግድ ሀይልን መጠቀም አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ የተፈጸመን ከባድ ወንጀል ለማጣራት ከተከሳሹ የአካል ናሙናን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝና ተጠርጣሪው ፍቃደኛ ባይሆን ምን መደረግ አለበት? የተፈጸመን አንድ የወንጀል ድርጊት ለማረጋገጥ የተጠርጣሪነረ መኖርያ ቤት መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝና ተከሳሹ ወደቤቱ ለማስገባት እንቢተኛ ሆነ ቢገኝ ምን መደረግ አለበት? እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ጠያቄዎችን በማንሳት ጉዳዩን ስንመረምረው፤በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ የሚለው ሀረግ የተከሳሽን የእምነት ቃል ለማግኘት ከሚደረገው ተግባር ጋር የተያያዘ እንደሚሆን መገመት አያዳግትም፡፡

(መ) የስሚ ስሚ (hearsay) - በፍትህ ብሄርም ሆነ በወንጀል ለማስረዳት ሚቀርብ ምስክር አለ ወይንም የለም፣አልተደረገም ወይም ተደረጓል፣ወ.ዘ.ተ. ለሚለው አከራካሪ ነጥብ በራሱ የስሜት ህዋሳት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተገነዘበውን ማስረዳት አለበት፡፡ በዚህ አይነት መልኩ ያለተገነዘበውን ከሌላ ወገን የሰማውን መነሻ በማድረግ የምስክርነት ቃል መስጠት አይችልም፡፡ እንደዚህም በሆነ ጊዜ ማስረጃው የሚቀርብበት ተከራካሪ ወገን የምስክሩ አስረጅነት የስሚ ስሚ መሆኑን በመጥቀስ መቃወሚያ ማቅረብ ይችላል፡፡

በመርህ ደረጃ የስሚ ስሚ ማስረጃ ሊቀርብ አይችልም ቢባልም፤አንዳንድ ጉዳዮችን በሚመለከት እንዲቀርብ የሚፈቀድበት ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡ በኮመን ሎው የህግ ስርአት ተከታይ አገሮች ማስረጃው ተቀባይነት የሌለው ሲሆን፤የሞት ሰአት ኑዛዜን (dying declaration) በሚመሳሰሉ ጉዳዮች ግን ቀርቦ እንዲሰማ ይፈቀዳል፡፡ በሀገራችንም የህግ ስርአት የስሚ ስሚ ማስረጃ ተቀባይነት አለው ወይንስ የለውም የሚለው በህግ በግልጽ ተቀምጦ ባይገኝም በተግባር ተቀባይነት የለውም በሚል እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል የሽብርተኝነትን ወንጀል በተመለከተ ግን የስሚ ስሚ ማስረጃ ተቀባይነት እንዳለው በአዋጅ ቁጥር 652/2001 ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በሀገራችን በመርህ ደረጃ የስሚ ስሚ ማስረጃ ተቀባይነት ከተባለም፤በተለየ ሁኔታ ሽብርተኝነት ወንጀልን በሚመለከት መቅረብ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ከሽብርተኝነት ወንጀል ውጭ ባሉ ወንጀሎች የስሚ ስሚ ማስረጃ ቢቀርብ ማስረጃው የቀረበበት ወገን መቃወም ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 137 (1) እና የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 263 (1) እንደተመለከተው ምስክሩ በቀጥታም ሆለ በተዘዋዋሪ የሚያውቀውን መመስከር ይችላል ስለሚል፤በተዘዋዋሪ የሚለው የስሚ ስሚንም ሊጨምር ስለሚችል፤በሌሎች የወንጀል ጉዳዮችም የስሚ ስሚ ማስረጃን ለመጠቀም ህጉ አይከለክልም የሚል የመከራከሪ ሀሳብ አለ፡፡ ይህ ሀሳብ ትክክል አይደለም በማለት የሚቀርበው ክርክር ደግሞ እስከዛሬ በተግባር በነበረው አተረጓጎም በተዘዋዋሪ የሚለው የስሚስሚ ማስረጃን እንደማይጨምር ተደርጎ ነበር ሲሰራ የነበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተዘዋዋሪ የሚለው የስሚ ስሚ ማስረጃን የሚጨምር ቢሆን ለምን ሽብርተንነትን በሚመለከት አዲስ ድንጋጌ ማውጣት አስፈለገ? በማለት ክርክር ይቀርባል፡፡

**(ሠ) ሀሳብን መጠየቅ-** በማስረጃነት የሚቀርቡ ምስክሮች ኤክስፐርቶች ሊሆኑ ወይንም ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ በቀረበው ፍሬ ነገር ላይ የራሳቸውን አስተያየት መስጠት የሚችሉት የኤክስፐርት

ምስክር ከሆኑ ብቻ ነው፡፡ የቀረቡት ምስክሮች ኤክስፐርት ያልሆኑ ምስክሮች ከሆኑ ግን የራሳቸውን አስተያዬት ወይም ግምት ማቅረብ አይችሉም፡፡ ኤክስፐርት ያልሆኑ ምስክሮች በስሜት ህዋሳቶቻቸው በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ ያወቁትን ወይም የተረዱትን ብቻ ነው እንዲገልጹ የሚፈለገው፡፡

በአማራ ክልል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኘ በምሰራበት ወቅት የዘር ማጥፋት ወንገል ሰርተዋል ተብለው በተከሰሱ ሰወች ላይ አቃቤ ህግ ከሚያቀርባቸው ምስክሮች ውስጥ አንዳንዶቹ እንዲመሰክሩ የሚጠሩት ተገደሉ የተባሉ የተባሉት ሰወች በትክክል መገደላቸውን ለማስረዳት ነው፡፡ ምስክሮቹም ቀርበው የሚያስረዱት ሚኞች በመንገድ ላይ ተገድለው ተጥለው ማየታቸውን ነው፡፡ ለነዚህ ሰዎች በተከራካሪ ወገኖች ከሚቀርቡ ጥያቄዎች አንዱ ቶችን ማን የገደላቸው ይመስላችኋል የሚል ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በቅርቡ በሶስት ሴቶች ላይ በሌሊት የተፈጸመውን የዘረፋ ወንጀል ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ቀርበው ምስክርነት የሰጡ ምስክሮች ድርጊቱን የፈጸሙት በችሎት የቆሙት አራት ተከሳሾች እንደሆኑ ገልጸው አንድኛው ገጀራ ይዞ ፈንጠር ብሎ ከመቆም በስተቀር በእነሱ ላይ ያደረገው ነገር እንደሌለ አስረድተዋል፡፡ በተከሳሾች ተከላካይ ጠበቃ ከቀረበላቸው መስቀልኛ ጥያቄ አንዱ ገጀራውን የያዘው በተበዳዮቹ ላይ ጉዳት ለማድረስ ነው አይደል? በማለት ሲጠይቅ ምስክሮቹ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ አስረድተዋል፡፡

ከላይ በዘር ማጥፋትና በዘረፋ ወንጀሎች የታየውን ስንመለከት ምስክሮቹ ሊሰጡት የሚችሉትን አስተያየት ዳኞችን ጨምሮ ማንኛውም ሰው የራሱን ግምት ማስወመጥ ስለሚችል የምስክሮቹን አስተያየት በማስረጃነት ልንመዝነው አንችልም፡፡ በመሆኑም ኤክስፐርት ላለሆኑ ምስክሮች የግል አስተያየትን በሚመለከት የሚቀርብ ጥያቄን መቃወም ይቻላል፡፡ በኤክስፐርትነት ለማስረዳት የሚቀርቡ ምስክሮችንም ቢሆን ከሞያቸው ጋር

የተያያዘን ሞያ ነክ ጥያቄን እንጅ፤ በሰውነታቸው እንደማንኛውም ሰው በሚያውቁት ነገር ላይ አስተያየት መጠየቅ አይቻልም፡፡

(ረ) ከላይ በዝረዝር የተመለከትናቸው የመቃወሚያ ነጥቦች ዋና ዋና ሲሆኑ፤ሌሎች በመቃወሚያነት ሊነሱ የሚችሉ ነጥቦችም አሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ብዙ ጥያቄዎችን በአንድ ጊዜ አጣምሮ መጠየቅ (compound questions)
- ግልጽ ያልሆነ ጥያቄ ማቅረብ (vague/too general/not specific)
- ምስክሩ ያላለውን መጥቀስ (misstating the evidence)
- በመደጋገም መጠየቅ (repetitive)
- ከምስክር ጋር መከራከር (aruementative questions)
- ማምታታትና አቅጣጫ ማሳት (confusing/misleading)
- ምስክሩ መጠየቅ የማይገባወን መጠየቅ (evidence excluded because of privilege)
- መሰረት የሌለው ጥያቄን ማቅረብ (no foundation)
- አለአግባብ አስረጅነትን ዋጋ ማሳጣት (improper impeachement)
- ተገቢ ያልሆነ ድጋሚ ጥያቄ ማቅረብ (improper re-examination)
- እነዚህንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ምክንያታዊ በመሆን ማቅረብ ይቻላል፡፡

ከላይ በዝርዝር የተመለከቱት የመቃወሚያ ነጥቦች ከባህሪያቸው መገንዘብ እንደሚቻለው በማንም ምክንያታዊ በሆነ ሰው እይታ ተቃውሞ ባይቀርብባቸውና በዝምታ ቢታለፉ ውሳኔ ለሚሰጠው አካል ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ምን ያህል አስቸጋሪ ሆኔታን እንደሚፈጥሩ መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት አጠቃላይ ግንዛቤ ለመውሰድ ቢያስፈልግ በተመሳሳይ መመዘኛ ሲታዩ ተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ እስከአደረሱ ድረስ በዚህ ጽሁፍ በዝርዝር ያልተቀመጡ ሌሎች ነጥቦችንም በቃወሚያነት ማንሳት ይቻላል፡፡

## ዘጠኝ

### አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች

1 (ሀ) የፍትሀ ብሄር ስነስርአት ህግ ቁጥር 258 ‹‹ክስን የመክፈትና ሙግትን የመጀመር መብት ያለው ከሳሽ፡፡ ነገር ግን ተከሳሹ ከሳሽያቀረበበትን ክስ አምኖ፤ህግ ወይንም ሌላ ፍሬ ነገር፤ወይም በከሳሽ አቤቱታ ያልተመለከተ አዲስ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ሲሆን ሙግቱን የሚከፍተው ወይም ክርክሩን የሚጀምረው ተከሳሹ ይሆናል፡፡››

የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 259 ‹‹ ሙግቱን ለመክፈት መብት ያለው ወገን የክሱን መግለጫ ወይም የከሳሽነት ቃሉንበመስጠት፤መመስረት የሚገባውን ጭብጥና ያቀረበውን ክስ የሚደግፍለትን ማስረጃ ያቀርባል፡፡ ››

‹‹ ሌላው ተከራካሪ ወገን ደግሞ ለመከላከያ የሚሆነውን መክፈቻና ፤የመከላከያ ቃል እንዳለው ካስረዳ በኋላ፤ስለጠቅላላው ክስ ያለውን አስተያየት ለፍርድ ቤቱ የቀርባል፡፡››

(ለ) የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 136 ‹‹ የተከሳሹ እምነት ክህደት በመዝገብ ከገባ በኋላ፤አቃቤ ህጉ ክሱን ሲከፍት ሊያስረዳ ያቀረበውን ክስና የሚያቀርበውን ማስረጃ አይነት በአጭሩ ይገልጻል፤ይህንንም በትክክል ያለአድሎ ማመልከት አለበት፡፡››

የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 142 ‹‹ ተከሳሹ ወይንም ጠበቃው መከላከያውን መክፈትና በመከላከያው ሊያስረዳው ያቀረበውን ማስረጃ በመግለጽ አጭር መግለጫ ይሰጣል፡፡ ››

2 (ሀ) የፍትሀ ብሄር ስነስርአት ህግ ቁጥር 263 (1) ‹‹ ምስክሩ የመጀመርያ ቃሉን ሲሰጥ የሚቀርብለት ጥያቄ ጭብጡን የሚመለከትና በቀጥታ ወይም በሌላ መንገድ በሚያውቀው ወይም ሊያውቀው በሚችለው ነገር ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆን አለበት ፡፡››

‹‹ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደ በቀር በማናቸውም ሁኔታ ለሚመሰክረው ጉዳይ መሪ የሚሆን ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም፡፡ ››

(ለ) የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 136(3) ‹‹ አቃቤ ህጉ ዋናውን ጥያቄ ጠይቋቸው ከፈጸመ በኂላ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው መስቀልኛ ጥያቄ ይጠይቃቸዋል፡፡ ››

የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 137(1) ‹‹ በዋና ጥያቄ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ውሳኔ ስለሚሰጥበት ፍሬ ነገር ተገቢ የሆኑትንና በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ምስክሩ ስለሚያውቃቸው ፍሬ ነገሮች ብቻ ናቸው፡፡ ››

እንደ ነገሩ ሁኔታ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ወይም አቃቤ ህጉ ሳይፈቅዱ የመምራት ጥያቄ ምስክሩ አይጠየቅም፡፡ ››

3 (ሀ) የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 263 (3) በመስቀልኛ የሚቀርበው ጥይቄ ምስክሩ በመጀመርያ ጊዜ የሰጠው የምስክርነት ቃል የተሳሳተበትን፣አሰት ነው የሚባልበትን ወይም አጠራጣሪ መስሎ የተገመተበትን ነጥብ ፍርድ ቤቱ እንዲረዳው የማድረግ አላማ ያለው መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም በመስቀልኛ ጥያቄ ላይ ምስክሩን መምራት ይቻላል፡፡ ››

(ለ) የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 137 (3) ‹‹ መስቀልኛ ጥያቄ በዋና ጥያቄ በተሰጠው መልስ ውስጥ ያለውን የስህተት ቃል፣የሚያጠራጥር ቃል ወይም እውነት ያልሆነውን ቃል ለፍርድ ቤቱ ለመግለጽና ለማስተባበል የሚደረግ ጥያቄ ነው፡፡ የመምራት ጥያቄዎችን በመስቀልኛ ጥያቄ መጠየቅ የረቻላል፡፡ ››

(ሐ) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 21 (4) ‹‹ የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸውን ማናቸውም ማስረጃ የመመልከት፣የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መመብት አላቸው፡፡ ››

4 (ሀ) የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 261 (4) ‹‹ ስለጉዳዩ ማብራራትና ስለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ መስሎ የታየው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ምስክሩን ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ››

የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 264 (1) ‹‹ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ነገሩን የሚያውቅ ወይም ለክርክሩ ጠቃሚ የሆነ ጽሁፍ በእጁ የሚገኝ ሰው ፍርድ ቤት ቀርቦ የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ወይም በእጁ የሚገኘውን ጽሁፍ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል፡፡ ››

የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 264 (2) ‹‹ እንዲሁም ተከራካሪ ወገኖች ካቀረቧቸው ምስክሮችና ከራሳቸውም በቀር፤ሌሎች ምስክሮች መስማት ጠቃሚ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከገመተው በሚወስነው ቀነ ቀጠሮ ተጠርተው የምስክረነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ወይም በእጃቸው ያለውን ሰነድ እንዲያቀርቡ የመጥሪያ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ ››

(ለ) የወነወጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርአት ቁጥር 136 (4) ‹‹ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት አስፈላጊ መስሎ ሲታየው ፍርድ ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ምስክሩን ማናቸውንም አይነት ጥያቄ ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ››

የወንጀለና መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 143 (1) ‹‹ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ምስክርነቱ አስፈላጊ ከመሰለው ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ማናቸውንም ምስክር መጥራት ይችላል፡፡ ››

5 (ሀ) የፍትሀ ብሄር ስነ ስርአት ህግ ቁጥር 273 ‹‹ የማስረጃው መሰማት ስርአት ተጣርቶ ሲፈጸም በዚህ ህግ ቁጥር 259 የተመለከተው የፍርድ መቀበያ የሚሆነው ማጠቃልያ ሀሳብ ከቀረበ በኋላ ፍርድ ቤቱ የፍርድ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ››

(ለ) የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 148 (1) ‹‹ የመከላከያ ማስረጃ ማስረጃ መሰማት ከተፈጸመ በኋላ ስለህጉና ስለነገሩ አቃቤ ህጉ ይናገራል፡፡ ››

የወነወጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት ቁጥር 148 (2) ‹‹ ከዚህ በኋላ ተከሳሹ ወይም ጠበቃው ስህጉና ስለነገሩ ማስረጃ ሁኔታ ይናገራል፡፡ እሱም ሁል ጊዜ የመጨረሻ ንግግር ያደርጋል፡፡ ››

6 (ሀ) የተሸሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የስነ ስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 44

ንኡስ ቁጥር 1 በአቃቤ ህግ ወይንም በመከላከያ ምስክርነት የቀረበ ማንኛውም ሰው፤በምስክርነት በተጠራበት ጉዳይ እውነቱን ለመናገር ባለመፈለግ ቀድሞ ከሰጠው የምስክርነት ቃል የሚቃረን የምስክርነት ቃል የሰጠ እንደሆነ፤ፍርድ ቤቱ ምስክሩን ያቀረበውን ወገን መሪ ጥያቄ እንዲጠይቅ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

ንኡስ ቁጥር 2 ፍርድ ቤቱ መሪ ጥያቄ እንዲጠየቅ ከመፍቀዱ በፊት ተቃራኒ የምስክርነት ቃል የሰጠ መሆን አለመሆኑን ምስክሩን ይጠይቀዋል፡፡ምስክሩ ተቃራኒ ቃል መስጠቱን ከተቀበለ መሪ ጥያቄ የፈቅዳል፡፡

ንኡስ ቁጥር 3 ምስክሩ ተቃራኒ የምስክርነት ቃል መስጠቱን የካደ እንደሆነ ፍርድቤቱ ምስክሩ ተቃራኒ ቃል መስጠት አለመስጠቱን ይወስናል፡፡

ስም……..አስካለች ምትኬ

ፆታ……...ሴት

ዕድሜ……25

የትውልድ ዘመን…… 1981 ዓ/ም

ሀይማኖት…………… ክርስትያን

ስራ…………………... የቀን ሰራተኛ

ዜግነት……………….. ኢትዮጵያዊ

አድራሻ………………. ቦል ክፍለ ከተማ ቀበሌ 45 የቤ.ቁ.አዲስ

እኔ ስምና አድራሻዬ ከላይ የተመለከተው ዛሬ ጥር 12 ቀን 2005 ዓ/ም ከጠዋቱ 2ሰአት ለክፍለ ከተማው ፖሊስ የሚከተለውን ቃሌን በትክክል ሰጥቸቻለሁ፡፡

ቀኑ ጥር 11 ቀን 2005 ዓ/ም ነው ፡፡ ቦታው የጥምቀት በአል የሚከበርበት ነው፡፡ ወደ በአሉ ስፍራ የሄድኩት ከጓደኛዬ አበበች ከበደ ጋር ነው፡፡ በበአሉ ቦታ ብዙ ህዝብ ነበር፡፡ አሁን ስሟን የማላስታውሳት የጓደኛዬ አበበች ከበደ ጓደኛ ሁነኛው ዘለቀ ከተባለ ሰው ጋር አስተዋወቀችን፡፡ እበአሉ ስፍራ ሁላችንም ስንጫዎት እስከ ምሽቱ 2 ሰአት ድረስ ቆይተናል፡፡ ከመሸ በኋላ እኔ ወደ ቤት ለመሄድ ስለፈለኩኝ ሁሉንም ተሰናበትኳቸው፡፡ ቤቴ ከበአሉ ቦታ በግምት 30 ደቂቃ ያህል ያስኬዳል፡፡ መንገድ ስጀምር ሁነኛው ዘለቀ ልሸኝሽ በማለት ተከተለኝ፡፡ አብረን ስንጓዝ ስለበአሉ ሁኔታ እያወራን ነበር፡፡ በመጨረሻም እመኖርያ አካባቢዬ ስደርስ ሁነኛውን ደህና እደር በማለት ስሰናበተው፤እጄን ያዝ አደረገኝና ለምን አብረን እቤትሽ አናድርም አለኝ፡፡ እኔም የፍቅር ጓደኛ እንዳለኝ በመንገር ፍቃደኛ አለመሆኔን ነገርኩት፡፡ እሱም በጣም ተቆጣ፡፡ ትቸው ወደቤቴ በፍጥነት መራመድ ጀመርኩ፡፡ ዞር በማለት ስመለከት ቆም

ወደእኔ ይመለከት ነበር፡፡ እቤት እንደገባሁ እግሬን ታጥቤ ወደመኝታዬ ሄጄ ተኛሁ፡፡ በግምት አንድ 30 ደቂቃ እንደተኛሁ ድምጽ ስለሰማሁ ባንኜ ተነሳሁ፡፡ ስባንን በሩ ተከፍቶ አንድ ሰው ወደእኔ ሲጠጋ አዩሁት፡፡ ለመጮህ ስሞክር እንዳትጮሂ ህይወትሽን አጠፋዋለሁ በማለት አስፈራራኝ፡፡ ወደእኔ በመጠጋትም በሀይል አልጋው ላይ አጋደመኝ፡፡ ከዚያም በሀይል በማስገደድ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈጸመብኝ፡፡ የፈለገውን ካደረገ በኂላ ከቤት ወጥቶ ሄደ፡፡ የቤት አከራዩ ወ/ሮ አረጋሽ ጉርሙ ሳለቅስ ሰምተው እኔ ጋር መጡ፡፡ የሆነውን ሁሉ ነገርኳቸው፡፡እሳቸውም አጽናንተውኝ ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡ በማግስቱ ጠዋት ለጓደኛዬ ለአበበች ከበደ ሁነኛው ዘለቀ እንደደፈረኝ ነገርኳት፡፡ አብረን በመምጣት ለፖሊስ አመለከትን፡፡ ሁነኛው መሆኖን ያወቅሁት በድምጹና በሚያጤሰው ሲጋራ ሽታ ነው፡፡

ተነቦልኝ ትክክለኛ ቃሌ መሆኑን በማመን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የመርማሪው ፊርማ የተበዳይ ፊረማ

ስም………………. ወ/ሮ አረጋሽ ጉርሙ

ፆታ………………. ሴት

ዕድሜ……………. 65 ዓመት

ሀይማኖት…………. ክርስትያን

ስራ…………………. ባለትዳር

ዜግነት……………… ኢትዮጵያዊ

አድራሻ……………… ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 45 የቤ.ቁ.አዲስ

እኔ ስሜና አድራሻዬ ከላይ የተጠቀሰው ዛሬ ጥር 12 ቀን 2005 ዓ/ም ክፍለ ከተማው ፖሊስ በመቅረብ የሚከተለውን የምስክርነት ቃሌን ሰጥቻለሁ፡፡

ወ/ሪት አስካለች ምትኬ የምትኖረው የእኔቤት ተከራይታ ነው፡፡ የጥምቀት እለት ማታ በግምት 4 ሰዓት ይሆናል ስታለቅስ ሰምቸ ምን ሆና እንደሆነ ላያትና ልጠይቃት ወደቤትዋ ሄድኩ፡፡ ሳንኳኳ ማነው ስትል እኔ ነኝ አልኳት፡፡ ከፈተችልኝና ስገባ እንዳልሆነች ሆና ሰውነቷ ተጎሳቁሎ፣አይኗ አብጦና ቀሚሷ ተቀዳዶ አየኋት፡፡ ምን አገኘሽ በማለት ጠየቅኋት፡፡ እያንቀጠቀጣትና እያለቀሰች ሁነኛው የተባለ ሰው መጥቶ እንደደፈራት ነገረችኝ፡፡ እኔም ሲነጋ ለፖሊስ እንደምንከስ ነግሪያት አጽናንቻት ወደቤቴ ተመለስኩ፡፡ ከቤት ወጥቸ ወደእሷ ቤት ስሄድ አንድ ሰው ከሷ ቤት አቅጣጫ ወደዋናው በር ሲሄድ አይቻለሁ፡፡ ቁመቱ እረዘም ያለና መካከለኛ ውፍረት ያለው ነበር፡፡

ተነቦልኝ ትክክለኛ ቃሌ መሆኑን አረጋግጨ ፈርሚያለሁ፡፡

የመርማሪው ፊርማ　　　　　　　　　　　　　የምስክር ፊረማ

ስም………………… ወ/ሪት አበበች ከበደ

ፆታ………………… ሴት

ዕድሜ……………… 28 ዓመት

ሀይማኖት…………… ክርስትያን

ስራ………………….. ስራ ፈላጊ

ዜግነት………………. ኢትዮጵያዊ

አድራሻ……………….. ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 45 የቤት ቁጥሩን አላውቀውም

እኔ ስሜና አድራሻዬ ከላይ የተጠቀሰው ዛሬ 12 ቀን 2005 ዓ/ም ክፍለ ከተማው ፖሊስ ቀርቤ የሚከተለውን የምስክርነት ቃል ሰጥቻለሁ፡፡

ወ/ሪት አስካለች ምትኬ ጓደኛዬ ናት፡፡ ትናንት ጥምቀት በአል የሄድነው አብረን ነበር፡፡ እበአሉ ላይ አብረን እስከ ምሽቱ በግምት 2 ሰአት ድረስ አብረን ነበርን፡፡ ከሁለት ሰአት በኋላ እሷ ወደቤቷ ሄደች፡፡ ወደቤቷ ስትሄድ ልሸኝሽ በማለት ሁነኛው አብሯት ሄዷል፡፡ ሁነኛው ዘለቀ እበአሉ ስፍራ እኔንም እሷንም የተዋዎቀን ሰው ነው፡፡ በማግስቱ ጥዋት እኔ ቤት መጣች፡፡ ሳያት አይኗ በጣም አብቷል፡፡ አይኗ ያበጠው ስላለቀሰችበት ነው፡፡ እኔም ጋር ስትመጣ እያለቀሰች ነበር፡፡ ምን ሆንሽ በማለት ጠየቅኳት፡፡ ሁነኛው አቤቴ ድረስ መጥቶ አስገድዶ ደፈረኝ በማለት ገለጸችልኝ፡፡ እኔም ካረጋገኋት በኋላ ወደፖሊስ ጣቢያው መጣን፡፡

ተነቦልኝ ትክክለኛ ቃሌ መሆኑን አረጋግጬ ፈርሚያለሁ፡፡

የመርማሪ ፊርማ የምስክር ፊርማ

ስም………………. ሁነኛው ዘለቀ

ፆታ……………….. ወንድ

ዕድሜ…………….. 40 ዓመት

ሀይማኖት………… ክርስትያን

ስራ……………….. የቀን ሰራተኛ

ዜግነት……………. ኢትዮጵያዊ

አድራሻ……………. ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 45 የቤት ቁጥር የለውም፡፡

እኔ ስሜና አድራሻዬ ከላይ የተጠቀሰው ተከሳሽ ክፍለከተማው ፖሊስ ጽህፈት ቤት ቀርቤ ቃሌን ለመስጠት እንደማልገደድ፤ፈቅጀ የመሰጠው ዋል ደግሞ ከተከሰስኩ በማስረጃነት እንደሚቀርብብኝ ከተነገረኝ በኋላ የሚከተለውን ቃሌን ሰጥቻለሁ፡፡

አስካለች ምትኬ ጋር የተዋወቅነው የጥምቀት በአል እለት ነው፡፡ እበአሉ ላይ አብረን ውለናል፡፡ በዚህ አመት ጥምቀት ነው፡፡ ሲመሽ አብረን ከበአሉ ስፍራ በመውጣት ወደእሷ ቤት ሄደናል፡፡ በመንገድ ላይ ስንሄድ እጣወራንና እየተጫወትን ነበር፡፡እየሄድን እያለን እንደምወዳት ገልጬላት አብረን እንድናድር ጠየቅኋት እንደማፈር አለችና ትንሽ ካቅማማች በኋላ ፍቃዷን ገለጸችልኝ፡፡ አብረን እቤቷ ገባን፡፡ ትንሽ ስንጫወት ቆይተን ስለደከመን ተኛን፡፡ ለሊት ላይ እፈራለሁ ስላለችኝ በሌሊት ከቤት ወጥቸ ሄድኩኝ፡፡ በእሷ ላይ የፈጸምኩት ሌላ ነገር የለም፡፡ ተነቦልኝ ትክክለኛ ቃሌ መሆኑን አውቄ ፈርሚያለሁ፡፡

የመርማሪ ፊርማ                                        የተከሳሽ ፊርማ

ስም……………………ኮንስታብል አበራ ኩምሳ

ፆታ…………………… ወንድ

ዕድሜ………………… 30 ዓመት

ሀይማኖት…………….. ክርስትያን

ስራ……………………. መርማሪ ፖሊስ

ዜግነት……………….. ኢትዮጵያዊ

አድራሻ……………….. ቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ

እኔ ስሜና አድራሻዬ ከላይ የተጠቀሰው የፖሊስ ሰራዊት ባልደረባ ቦሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ ቀርቤ የሚከተለውን የምስክርነት ቃል ሰጥቻለሁ፡፡

እለቱ ጥሪ 12 ቀን 2005 ዓ/ም ነው፡፡ አስካለች ምትኬ የተባለች የግል ተበዳይ ቀርባ ሁነኛው ዘለቀ የተባለ ሰው አስገድዶ እንደደፈራት ገልጻ ክስ አቀረበች፡፡ በአቀረበችው አቤቱታ መሰረት ቃሏን ተቀበልኳት፡፡ ከሷም ቃል በመነሳት ወ/ሮ አረጋሽ ጉርሙንና ወ/ሪት አበበች ከበደን የምስክርነት ቃላቸውን እነዲሰጡኝ ጠርቻቸው ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተውኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የወንጀሉ ድረጊት ተፈጸመ በተባለበት ቤት ከስራ ባልደረባዬ ከኮንስታበል ገብረመድህን ግደይ ጋር አብረን በመሄድ እንዳንድ መረጃዎችን አሰባስበናል፡፡ ከሰበሰብናቸው ማስረጃዎች ውስጥ አንዱ በደም የተነካካ እና የተቀዳደደ ቀሚስ ነው፡፡ ቀሚሱ የግል ተበዳይ የእኔ ነው ያለችህን ሲሆን በቀሚሱ ላይ ያለው ደም ደግሞ ግል ተበዳይ ከተጠርጣሪው ጋር ስትታገል ፊቱን ስትሟችረው ፊቱ በመድማቱ እንደሆነ ነግራናለች፡፡ በዚሁ መሰረት ተተርጣሪው በቁጥጥር ስር በማድረግ የመረመርኩት ሲሆን ተይዞ በቀረበ ጊዜ እፊቱ ላይ የመቦጫጨር ምልክት ነበረበት፡፡ ተጠርጣሪው የተያዘው በሶስተኛው ቀን ነበር፡፡

ትክክለኛ ቃሌ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የምስክር ፊርማ

## <u>ዋቢ ጽሁፎች ( bibiliography )</u>


1. Steven Lubet,<u>Modern Trial Advocacy</u>, third edition,2010,USA
2. James W.Jeans,<u>Trial Advocacy</u>,Second edition,1993,USA
3. <u>Tips for excuting a winning croo-examination</u>:These materials are excerpted from On trial advocacy skill law and practice by Geoffrey D.E.Adair,QC, (Toronto: butterworth,2004)
4. <u>The art of Direct examination</u>: These materials were originaly prepared by Teresa R.Mtchell-Banks,QC, Crown Council,criminal appeals and special prosecutions,Vancouver,BC,for tha CLEBC publication advocacy conference (November 2001)
5. የ1958 <u>የኢትዮጵያ የፍትሀ ብሄር ስነስርአት ህግ</u>
6. የ1954 <u>የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት</u>
7. የ1987 <u>የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት</u>
8. <u>International covenant on civil and political Rights</u>, G.A.Res.2200A (xxl),21UN. GAOR supp.(No.16) At52,UN Doc.A/6316 (1966)
9. የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የስነስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997
10. የኢትዮጵያ የፀረ ሽብርተኝነት ህግ አዋጅ ቁጥር 652/2001 ዓ/ም